

OROMIA EDUCATION BUREAU

ይህ ጥራዝ ለአስረኛ ክፍል የተዘጋጀ ሲሆን በተማሪው መፅሀፍ ከምዕራፍ ስድስት እስከ ምዕራፍ አስር ድረስ የተካተቱትን ዋና ዋና ይዘቶች የሚመለከቱ አጫጭር ማስታወሻዎች፣ መልመጃዎችና ጥያቄዎችን የያዘ ነው።

አዘጋጅ፡ አበበች ገብሩ ጨፌ

Email: abegebru133@gmail.com

0917723897

Ethio Students (Grade 9-12) telegram channel

ሚያዚያ 2012 ዓ.ም.

ኦሮሚያ ኢትዮጵያ

ይህ ጥራዝ ለአስረኛ ክፍል የተዘጋጀ ሲሆን ከምዕራፍ ስድስት እስከ ምዕራፍ አስር ድረስ የተካተቱትን ይዘቶች የሚመለከቱ አጫጭር ማስታወሻዎች፣ መልመጃዎችና ጥያቄዎችን የያዘ ነው።

በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙ ዝርዝር ይዘቶች

- ግጥም
- ምዕላድ
- የቃላት ቀጥተኛ ፍች
- የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች
- ድርብና ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ
- አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋት
- ስዕላዊ ድርሰት
- ምሳሌያዊ አነጋገር
- ቃላዊ ግጥም
- ሐረግ
- የዓረፍተ ነገር ስልቶች
- ሊጣዊ አነጋገር
- ጅምር ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ማሟላት
- ቅኔ

ዝርዝር ዓላማዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች፡-

- የግጥምን ምንነት ትገልፃላችሁ።
- የግጥምን ባህሪያት ታብራራላችሁ።
- የግጥም ዓይነቶችን ለይታችሁ ትናገራላችሁ።
- በበቂ ምዕላድ ላይ የተጨመሩ ቅጥያዎችን ተግባር ትገልፃላችሁ።
- የቃላዊ ግጥም ይዘቶችን ትገልፃላችሁ።
- ድርብና ነጠላ ትዕምርተ ጥቅሶችን በተገቢ ቦታ ትጠቀማላችሁ።
- ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ሰብስባችሁ ትርጉማቸውን ታብራራላችሁ።
- አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋትን ተጠቅማችሁ ድርሰት ትፅፋላችሁ።
- ሐረጋትን መስርታችሁ ዓይነታቸውን ትፅፋላችሁ።
- ዓረፍተ ነገሮችን በስልታቸው ትመድባላችሁ።
- ለፊሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ትሰጣላችሁ።
- ጅምር ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ታሟላላችሁ።
- የቅኔን ህብረ ቃል ለይታችሁ በማውጣት ሰምና ወርቅ ችፍ ትሰጣላችሁ።

❖ ግጥም

- **ግጥም ምንነት**

ግጥም የሰው ልጅ ደስታና ሀዘኑን ምኞትና ተስፋውን፣ ትዝታና ራዕዩን የሚያስተላልፍበት የኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው።

- ስነ ግጥም በባህርይው የሰውን ስሜት መግዛት የሚችል፣
- በቃልና በፅሁፍ የሚገኝ ጥበብ ነው።
- ቃላዊም ነው
- ከስነ ፅሁፍ ሁሉ ረጅም ዕድሜ አለው።
- ግጥም በጥቂት ቃላት አማካኝነት ሰፊና እምቅ መልዕክትን የማስተላለፍሃይል አለው።
- ግጥም የሚናገር ስዕል ነው።

- በጥቂት ቃላት አማካኝነት ሰፊ ቃላት አምቆ ሀሳባችን፣ ረቂቅ ሀሳቦችን፣ ጥልቅ ስሜቶችን መግለፅ ይችላል፡፡ እነዚህን ስሜቶችን አግዝፎ አጉልቶና ተጨባጭነት አላብሶ መግለፅ መቻሉ ሳይሆን በሙዚቃዊው ቃናው የተደራሲን ስሜት መንካት የሚችል ነው፡፡

- **የስነ ግጥም ባህርያት**

ግጥም ከሌሎች የስነ ፅሁፍ ዘርፎች የሚለይበት የራሱ የሆኑ ባህርያት አሉት፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡-

1. **ምት**፡- ግጥም ምት አለው፡፡ ምት ማለት ሀረጎችን፣ ስንኞችን ለማንበብ የሚወስድብን የጊዜ እርዝማኔን ይመለከታል፡፡
   በአንድ ትንፋሽ በሚነበቡ የቃላት ስብስቦች መሃል ያለውን የተወሰነ የጊዜ መጠን መጠበቂያ ስልት ነው፡፡ልክ እንደ ልብ ትርታችን በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ስርዓቱን ጠብቆ ‹‹ድው … ድው … ድው…›› እንደሚለው ዓይነት ነው፡፡ ምትና ምጣኔ ያላቸው ትስስር ጥብቅ ነው፡፡
2. **ዜማ**፡- ይህ የሚፈጠረው የተስተካከለና የተከረከመ ምጣኔና ምት በሐረጉ ውስጥ በመኖሩ የተነሳ ነው፡፡ምጣኔ ከተዛባ ምቱ ምቱ ከተዛባ ደግሞ ዜማው የተዛባ ይሆናል፡፡
3. **ቁጥብነት** ፡- ግጥም ነገሮችን አይዘረዝርም ጠቋሚ እንጂ ዘርዛሪ አይደለም፡፡ በጥቂት ምርጥ ቃላት ሰፊ የሀሳብና የስሜት ይዘትን የሚያስተላልፍ ነው፡፡
   ግጥም ቁጥብ ነው ስንል ከቃላት አንፃር ነው፡፡
4. **እምቅነት**፡- ግጥም ዕምቅ ነው ጠቋሚ የሆኑትን ቃላት በውስጣቸው የያዙት ሀሳብና ስሜት በጣም ሰፊ ነው፡፡ ሀሳብን መበተን፣ መዝራት ሳይሆን በአንድነት ማሰባሰብ ማጨቅ አለበት ይህ ሲሆን ሀይል የኖረዋል፡፡ የግጥም እምቅነት ከሚያስተላልፈው መልዕክት (ሀሳብ) የሚመነጭ ነው፡፡
5. **ምጣኔ**፡- በግጥም ውስጥ የቀለማትን መጠን በሀረግ ውስጥ የምንመጥንበት (የምንለካበት) ዘዴ ምጣኔ ይባላል፡፡ ከዚህ እንደምንረዳው ግጥም ተለክቶ የሚያልቀው በሐረግ ውስጥ ሲሆን መለኪያው ደግሞ ቀለም መሆኑን ነው፡፡ ቀለም ማለት ምንድን ነው? ቀለም ማለት፡-

- ተናባቢና አናባቢ ድምፆች አንድ ላይ ሲመጡ የሚፈጥሩት የቋንቋ መዋቅር መለት ነው፡፡
  ለምሳሌ፡- ‹‹ና›› የሚለው በድምፃዊ አፃፃፍ ሲፃፍ /ንኣ/ የሚሉትን ድምፆች ይወክላል፡፡ ስለዚህ ‹‹ና›› በግጥም ውስጥ እንደ ቀለም ይቆጠራል፡፡
- አናባቢ ድምፅ ብቻውን ሲመጣ የሚፈጥረው የቋንቋ መዋቅር ነው፡፡
  ለምሳሌ፡- ኡ፣ ኣ፣ ኢ፣ …

- **የግጥም ዓይነቶች**

በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ የግጥም ምጠኔ ዓይነቶች ብዙ ቢሆኑም ለዚህ የክፍል ደረጃ መሰረታዊ የሆኑትን ሶስቱን ብቻ እንመለከታለን፡፡ የግጥም ዓይነቶችም እርስ በርስ የሚለያዩት ባላቸው የቀለም ምጣኔ መሆኑን ማስተዋል ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡
ማስታወሻ የግጥም ዓይነቶችን ለይተን ለማወቅ በምናደርገው ጥረት የቀለም ቆጠራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በፊት እንደተነጋገርነው ተነሽ እና ተረግጠው (ጠብቀው) የሚነበቡ ድምፆች እንደ ቀለም ይቆጠራሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ትኩረት ልናደርግባቸው የሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዮችን ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

- ✓ ሳድስ ሆሄ የቃል መጀመሪያ ሲሆን ስለሚረገጥ እንደ ቀለም ይቆጠራል፡፡
- ✓ ሳድስ ሆሄ የቃል መጨረሻ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ስለሚላላ እንደ ቀለም አይቆጠርም፡፡

- ✓ ሳድስ ሆሄ በቃል መካከል ሲገኝ እንደ አውዱ፣ እኛ እንደ ሰጠነው አፅንኦት ሁኔታ ቀለም ሊሆን ላይሆንም ይችላል።
- ✓ ‹‹አ›› ድምፅ የሚጎረድበት ሁኔታ ሲያጋጥመን በመጎረዱ ምክንያት እንደቀለም ላይቆጠር ይችላል።
  ምሳሌ፡- አትምጪ እ/ቤታችን
  በግጥም ውስጥ የሚገኙትን ቀለማት መሰረት በማድረግ የግጥም ዓይነቶች በሶስት ይከፈላሉ።
  እነሱም እንደሚከተሉት ይቀርባሉ

1. **የወል(ደንበኛ) ቤት፡-** ይህ የምጣኔ ዓይነት አብዛኛው ገጣሚ በተለይም ግጥም ለመግፍ ፍላጎት ያለው ሰው የሚጠቀምበት በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ ተራ ግጥም እየተባለ ይጠራል። ይህ የግጥም ዓይነት በሀረግ 6 በሀረግ 6 በስንኝ 12 ቀለማትን ይይዛል።
   ምሳሌ፡- አንቺ ልጅ አንቺ ልጅ የጎረቤታችን
   እናትሽ ተቆጡ አትምጪ ቤታችን
   ከላይ በምሳሌው የቀረበው ግጥም የቀለም አቆጣጠር ስንመለከት
   የመጀመሪያው ስንኝ አስራ ሁለት ቀለሞች አሉት እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡-
   ‹‹አ›› አናባቢ ስለሆነ ቀለም ነው።
   ‹‹ን›› ሳድስ ስለሆነ ቀለም አይደለም።
   ‹‹ቺ›› የአናባቢና የተነባቢ ቅንጅት ስለሆነ ቀለም ነው።
   ‹‹ል›› ሳድስ ብትሆንም የቃል መነሻ ስለሆነ ቀለም ነው።
   ‹‹ጅ›› ሳድስ ስለሆነ ቀለም አይደለም።
   ‹‹አ›› አናባቢ ስለሆነ ቀለም ነው።
   ‹‹ን›› ሳድስ ስለሆነ ቀለም አይደለም።
   ‹‹ቺ›› የአናባቢና የተነባቢ ቅንጅት ስለሆነ ቀለም ነው።
   ‹‹ል›› ሳድስ ብትሆንም የቃል መነሻ ስለሆነ ቀለም ነው።
   ‹‹ጅ›› ሳድስ ስለሆነ ቀለም አይደለም።
   ‹‹የ›› የአናባቢና የተነባቢ ቅንጅት ስለሆነ ቀለም ነው።
   ‹‹ጎ›› የአናባቢና የተነባቢ ቅንጅት ስለሆነ ቀለም ነው።
   ‹‹ረ›› የአናባቢና የተነባቢ ቅንጅት ስለሆነ ቀለም ነው።
   ‹‹ቤ›› የአናባቢና የተነባቢ ቅንጅት ስለሆነ ቀለም ነው።
   ‹‹ታ›› የአናባቢና የተነባቢ ቅንጅት ስለሆነ ቀለም ነው።
   ‹‹ች›› ሳድስ ነው ቢሆንም ጠብቆ ስለሚነበብ ቀለም ነው
   ‹‹ን›› ሳድስ ስለሆነ ቀለም አይደለም።
   በዚህ መሰረት ቀለም የሆኑትን ስንቆጥራቸው 12 ናቸው
2. **የሰንጎ መገን ቤት፡-** ይህ የግጥም ዓይነት ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ወኔን የሚቀሰቅሱ የፉከራ እና የጀግንነት ግጥሞችን እና የክራር ጨዋታዎቹን ለማድረግ የሚጠቀሙበት የምጣኔ ዓይነት ነው።
   ይህ የግጥም ዓይነት በሀረግ 5 በሀረግ 5 በስንኝ 10 ቀለማትን ይይዛል።
   ምሳሌ፡- አምሳ ቢወለድ አምሳ ነው ጉዱ
   ከተባረከ ይበቃል አንዱ።

3. **ቡሄ በሉ ቤት፡- ይህ የግጥም ዓይነት ልጆች የቡሄ በዓል ቀን ‹‹ቡሄ በሉ ለረጆች ሁሉ›› እያሉ ስለሚጫወቱ የተሰጠው ስያሜ ሲሆን ምጣኔውም በሀረግ ከአንድ እስከ አራት ቀለማት ይኖሩታል፡፡**
   ምሳሌ፡- ቡሄ በሉ
   ሆ
   ልጆች ሁሉ….
   መልመጃ አንድ

መመሪያ፡- የሚከተሉትን ግጥሞች ይነታቸውን ግለፁ

1. **ዱብ ዱብ ይላል እንደ በረዶ፣**
   በልጅነቱ በረሃ ለምዶ፡፡
2. **እስከ ጊዜው ድረስ እስኪሞላ ልኩ፣**
   የጀግና ፈረስ ነው የሰው ሁሉ መልኩ፡፡
3. **እዚያ ማዶ**
   ሆይ
   ጭስ ይጨሳል
   ሆይ…..
4. **አርበኞች መሞትን ማን አስተማራቸው፣**
   ታላቁ ጴጥሮስ ነው ባርኮ የሰጣቸው፡፡
5. **ውረድ እንውረድ ተባባሉና፣**
   አስደበደቡት አፋፍ ቆሙና

➢ ምዕላድ

➢ የምዕላድ ምንነት

ምዕላድ የምንለው ትርጉም አዘል የሆነና አነስተኛ ወደ ሆኑ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊሸነሸን የማይችል የመጨረሻው ንዑስ አሀድ ነው፡፡ ለምሳሌ (ልብ) በመጀመሪያ ትርጉም ያለው (አንድ የሰውነት ክፍልን የሚያመለክት) አሀድ ነው፡፡ ሁለተኛም ይህ አሀድ ወደ አነስተኛ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊከፋፈል አይችልም፡፡ እንክፈለው ብንል እንኳ የምናገኘው ትርጉም የሌላቸውን ድምፆች ነው፡፡ ስለዚህም ሁለቱን መስፈርት በማሟላቱ (ልብ) ምዕላድ ነው፡፡

በተመሳሳይ አኳሃን (ልባችን) የሚለውን አሀድ ደግሞ እንውሰድ፡፡ ይህ አሀድ በመጀመሪያ ትርጉም አዘል ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ምዕላድ ለመባል ከሱ በታች አነስተኛ ወደሆኑ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊከፈል አለመቻሉ መረጋገጥ አለበት፡፡ ይህንን ስናደርግ ቃሉ (ልብ) እና (-አችን) በሚል ሊከፋፈል የሚችል በመሆኑ ቃል እንጂ ምዕላድ አይደለም፡፡

በአንፃሩ (ልብ) እና (-አችን)የሚሉት አሀዶች ትርጉም ኖሯቸው ከነሱ ወዳነሱ ትርጉም አዘል ክፍሎች ልንከፋፍላቸው ስለማንችል ምዕላድ ናቸው፡፡

➢ የምዕላድ ዓይነቶች

ምዕላድ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡ እነሱም ነፃ ምዕላድ እና ጥገኛ ምዕላድ በመባል ይታወቃሉ፡፡

- ✓ **ነፃ ምዕላድ፡-** ራሳቸውን ችለው የቋንቋውን ተናጋሪ በሚገባ ሊያግባቡ የሚችሉ ቃላት ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ጦር፣ በግ፣ ዶሮ፣ ቤት፣ ... በነፃ ምዕላድ ምዕላድ ስር የሚመደቡ ናቸው፡፡ ነፃ ምዕላዶች ስርወ ቃል፣ ዋና ቃል፣ ዐምድ በመሳሰሉ የተለያዩ ስያሜዎችም ይጠራሉ፡፡
- ✓ **ጥገኛ ምዕላድ፡-** በራሳቸው ትርጉም ባይኖራቸውም በዋናው ቃል ላይ እየታከሉ ትርጉም ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ ጦር (-ኤ) ጦሬ

በግ (-ኤ) በጌ ወዘተ በማለት (-ኤ)ን የመሳሰሉ አናባቢዎች በማከል የእኔ የሚል ትርጉም እንዲሰጡ ማስፋፋት ይቻላል፡፡

እነዚህ ጥገኛ ምዕላዶች አገልግሎታቸውን መሰረት በማድረግ በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ እነሱም የእርባታ ምዕላድና መስራች ምዕላድ ናቸው፡፡

- ➢ **የእርባታ ምዕላድ፡-** በቃል ላይ ሲታከሉ ቃልን ወደ ሌላ የቃል ክፍልነት አይቀይሩም፡፡

ምሳሌ፡- በር-ኦች = በሮች ፣ በር - አችሁ = በራችሁ
ልብስ - ኦች= ልብሶች ፣ ልብስ - ኤ= ልብሴ፣ ልብስ - አችሁ= ልብሳችሁ
ከላይ የተጠቀሱት ቅጥያዎች ልብስ እንዲሁም በር በሚለው ቃል ላይ በመታከላቸውየቃል ክፍሉ ከስምነት ወደ ሌላ የቃል ክፍል አልተቀየረም፡፡ ቅጥያው ከመግባቱም በፊት ስም ነበር ቅጥያ ከገባበት ቦኋላም የቃል ክፍሉ ስም ነው

- ➢ **መስራች ምዕላድ፡-** በቃል ሲታከሉ ቃሉን ወደ ሌላ የቃል ክፍል ይቀይራሉ፡፡

ለምሳሌ፡- ልብ - አም= ልባም ፣ ሆድ - አም= ሆዳም፣ ዐመል - ኛ= ዐመለኛ

ከላይ የተጠቀሱት ቅጥያዎች በቅደም ተከተል ልብ፣ ሆድ፣ ዐመል በሚሉት ስሞች ላይ ሲታከሉ ልባም፣ ሆዳም፣ ዐመለኛ የሚሉ ቅፅሎችን መስርተዋል፡፡ እነዚህ ቅጥያዎች ከስሞች ቅፅሎችን መመስረት ስለቻሉ መስራች ቅጥያዎች ናቸው፡፡

- **የቅጥያ ምዕላዶች ተግባራት፡-** ጥገኛ ምዕላዶች በቃል ላይ ሲታከሉ የተለያየ ተግባር አላቸው፡፡ እነሱም
  - ➢ **ብዛትን ማመልከት፡-** በአማርኛ ቋንቋ ብዛት ለማመልከት የሚገቡ ጥገኛ ምዕላዶች ሁለት ናቸው፡፡ እነሱም፡- -ኦች እና -ዎች ናቸው፡፡

-ኦች፡- በሳድስ ድምፅ በሚጨርሱ ቃላት ላይ በመግባት ብዛትን ያመለክታሉ፡፡
ለምሳሌ፡- ላም-ኦች ላሞች፣ ከብት -ኦች ከብቶች ፣ በግ -ኦች በጎች
ም፣ ት፣ ግ ሳድስ መሆናቸውን ልብ በሉ፡፡

-ዎች፡- ከሳድስ ውጪ ባሉ ድምፆች በሚያልቁ ቃላት ላይ በመግባት ብዛትን ያመለክታል፡፡

ለምሳሌ፡- መኪና - ዎች መኪናዎች፣ ተማሪ -ዎች ተማሪዎች፣ ተላላኪ -ዎች ተላላኪዎች ልብ በሉ መኪና፣ ተማሪ፣ ተላላኪ ... የመሳሰሉ ቃላት (-አች) የአብዚ ቅጥያ የማወስዱበት ምክንያት በአማርኛ ቋንቋ ህግ ሁለት አናባቢዎች ተከታትለው ስለማይመጡ ነው፡፡

አማርኛ አልፎ አልፎ የግዕዝ ቋንቋ አበዛዝንም ሲከተል ይስተዋላል ለምሳሌ መምህራን ፣ ተግባራት ፣ ወዘተ የግዕዝን አበዛዝ የተከተለ ነው፡፡

- **ባለንብረትነትን አመልካች፡-**

ለምሳሌ፡- ኮት -ኤ ኮቴ፣ ኮት -ህ ኮትህ ፣ ኮት -ሽ ኮትሽ ፣ ኮት -አችሁ ኮታችሁ

ልብ በሉ ኮት በሚለው ቃል ላይ -ኤ፣ -ህ፣ -ሽ፣ -አችሁ በመግባታቸው ኮቴ ንብረትነቱ የማን እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

- **ያታን ማመልከት፡-**

ለምሳሌ፡- ልጅ - ኢት ልጂት ፣ ሙሽራ -ኢት ሙሽሪት መምህር -ት መምህርት

ከላይ በምሳሌው እንደተመለከትነው -ኢት እና -ት ያታን ያመለክታሉ፡፡

- **ታዋቂነትን (እምርነትን) ማመልከት**

ምሳሌ፡- ቤት -ኡ ቤቱ

ጨረቃ -ዋ ጨረቀዋ

- **ወገንን አመልካች፡-**

ምሳሌ፡- መንፈስ -አዊ መንፈሳዊ

ዘመን -አዊ ዘመናዊ

- **ዓይነትና ባህርይን ማመልከት**

ምሳሌ፡- እሾህ -አማ እሾሃማ

ድንጋይ -አማ ድንጋያማ

ሆድ -አም ሆዳም

- **ባለቤትና ቀጥተኛ ተሳቢን ማመልከት**

ምሳሌ፡- መታችኝ ባለቤት አመልካች -ች እሷ

ተሳቢ አመልካች -ኝ እኔን

መታቻችሁ ባለቤት አመልካች -ች እሷ

ተሳቢ አመልካች -ኣችሁ እናንተን

መልመጃ ሁለት

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት በነፃ ምዕላድና በጥገኛ ምዕላድ ከለያችሁ በኋላ የጥገኛ ምዕላዱን ተግባር ግለፁ፡፡

ተራ. ቁ	ቃል	ነፃ ምዕላድ	ጥገኛ ምዕላድ	የቅጥያ ምዕላዱ ተግባር
1.	ዘመናዊ			
2.	ኮታቸው			
3.	ድንጋያማ			
4.	ሙሽሪት			
5.	ክብቶች			
6.	ጨረቀዋ			
7.	ተግባራት			
8.	ልብሳችሁ			
9.	መስኮቶች			
10.	ኢትዮጵያዊ			

የቃላት ቀጥተኛ ፍች ማለት የቃሉ መዝገበ ቃላዊ ፍች ማለት ነው፡፡
የሚከተሉትን ቃላት መዝገበ ቃላዊ ቀጥተኛ ፍች በምሳሌነት ተመልከቱ
ሰደረ፡- ደረደረ፣ በረድፍ ስቀመጠ፣ በተራ አስቀመ
ማገጠ፡- ባለገ፣ ተበላሸ፣ ዋልጌ ሆነ
ወፈረ፡- ደነደነ፣ ሰባ፣ግዙፍ ሆነ፣ ለደለደ፣ አካል ጨመረ

መልመጃ ሶስት

1. ለሚከተሉት ቃላት ቀጥተኛ ፍች ስጡ
   - ሀ. ቀላ
   - ለ. ሰፈረ
   - ሐ. ሌጣ
   - መ. ሁከት
   - ሠ. መዘከር
2. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍች ስጡ
   - ሀ. ህይወት
   - ለ. ለጋስ
   - ሐ. ድሎት
   - መ. ከርዳዳ
   - ሠ. ቀትር

❖ ትዕምርተ ጥቅስ(‹‹ ››)

ሀ. የሌላን ሰው ሀሳብ እንዳለ ከወሰድን በትምርተ ጥቅስ ውስጥ ማስቀመጥ ይኖርብናል፡፡
ምሳሌ፡- ርዕሰ መምህራችን‹‹ለትምህርታሁ ትኩረት ስጡ›› ብለው መከሩን

ለ. የተውሶ ቃላት ሲጠቀም ባዕድነታቸውን ለማመልከት
ምሳሌ፡- ስልኩ ቀኑን ሙሉ ‹‹ቢዚ›› ነበር፡፡

ሐ. በዕሁፋችን ውስጥ በትርጉም የማናምንባቸውን አባባሎች ለይቶ ለማሳየት
ምሳሌ፡- ለትዳር የመረጡለት ‹‹የቤት ልጅ›› ነው፡፡

መ. በዕሁፍ ውስጥ የሁለት ገፀባህሪያትን ምልልስ(ንግግር) እየለዩ ለማሳየት
ምሳሌ፡- ‹‹መዕሀፉ ተገኘ››
‹‹አዎ››
‹‹የት?››
‹‹ከአልጋው ስር››...

❖ ነጠላ ጥቅስ(‹ ›)

በጥቅስ ውስጥ የሚገኝን ሌላ ጥቅስ ለማመልከት ይረዳል፡፡
አንድ ሰው የተናገረውን በሶስተኛ ወገን ሲነገር በነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ይቀመጣል፡፡
ምሳሌ፡- የትምህርት ቤታችን ርዕሰ መምህር፣ ‹‹ወጣቶች! ትምህርት የችግሮች ሁሉ መፍቻ ቁልፍ ነው፤ ሌኒን‹መማር መማር አሁንም መማር› እንዳለውሳትዘናጉ በርትታችሁ መማር ይኖርባችኋል፡፡›› በማለት ለተማሪዎች አስገነዘቡ፡፡

መልመጃ አራት

በሚከተሉት ዕሁፎች ውስጥ ድርብና ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ የሚገባው የቱጋ ነው

1. ምሁራን እንዲህ ብለዋል፤ ከማይምነት ያልተላቀቀ ህብረተሰብ በአመራረቱ፣ በአኗኗሩ፣ በአስተሳሰቡ ኋላ ቀር ነው፡፡ በተፈጥሮ ከመገልገል ይልቅ ለሷ እጁን የሰጣል፡፡
2. የእርሱ ስራ ሁሉ ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ እንደሚባለው ነው፡፡
3. ማለፊያ አሉ ፊታውራሪ ገንዘቡ ባደራ መልክ እኔ ዘንድ ይቀመጥልሃል፡፡ ካደራ የበለጠ ክቡርና ከባድ ነገር የለም መተማመን ከሌለ አደራ ሰጪም አደራ ተቀባይም አይኖርም ይል ነበር መክብብ፡፡
4. የወር ገቢው መቶ ሀምሳ የሚያጠፋው ሺ ከስልሳ የሚለውን ታስታውሳለህ? አለ፡፡
5. አዬ የአህያ ስጋ አልጋ ሲሉት አመድ አንቺ ደግሞ ወዴት ትሄጂ አማረሽ አሉ ወ/ሮ ድንቅነሽ

❖ አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት

አያያዥ ቃላት (ሀረጋት) ለብቻቸው ትርጉም አይሰጡም፡፡ ነገር ግን ተግባር አላቸው፡፡ ይኸውም፡-

- ከአንድ ሀሳብ ወደ ሌላ ሀሳብ ለመሸጋገሪያነት፣
- የቀደመውን ሀሳብ ከሚቀጥለው ማጠናከሪያ ጋር ለማቆራኘት፣
- አፍራሽ ወይም ተቃራኒ ሀሳቦችን ለማገናኘት፣
- ለቀደመው ሀሳብ ምክንያት ሰጪ ሀሳብን ለማስከተል፣
- የጊዜ ቅደም ተከተል ያላቸውን ሀሳቦች ለማያያዝ .....

ምሳሌ 1፡- በተጨማሪም
እንዲሁም
በዚህ ዓይነት } ተጨማሪ ሀሳቦችን የሚያያይዙ
ቀጥሎም

ምሳሌ 2፡-ይሁን እንጂ
የሆነ ሆኖ
ነገር ግን
ዳሩ ግን
} ተቃራኒ ሀሳቦችን የሚያያይዙ

ምሳሌ 3፡- በዚህ የተነሳ
በዚህ ሳቢያ
ስለዚህ
ምክንያቱም
} ምክንያት ሰጪ ሀሳቦችን ለማስከተል

ምሳሌ 4፡- ከዚህ ቦኋላ
ቀጥሎም
ወዲያው
በተመሳሳይ ጊዜ
} የጊዜ ቅደም ተከተል የሚጠብቁ ሀሳቦችን ለማያያዝ

ከላይ ያየናቸውን አያያዥ ቃላትና ሀረጋት በተወሰኑ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በማስገባት እንመልከት፡፡

- መምህራን ተማሪዎቻቸውን በእውቀት ከማበልፀግ **በተጨማሪም** በስነ ምግባር ማነፅ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- እግሩን በጣም አሞታል፤ **ይሁን እንጂ** ሩጫውን በአሸናፊነት አጠናቀቀ፡፡
- ነፋሱ ሀይለኛ ነው፤ **ስለዚህ** ሹራብ መደረብ አለብኝ፡፡
- ደውሉ ተደወለ፤ **ወዲያው** መምህሩ ገባ፡፡

መልመጃ አምስት

የሚከተሉትን ጥንድ ዓረፍተ ነገሮች አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አያይዟቸው፡፡

1. እኔ ቤት አፀዳለሁ፡፡ አንቺ ልብስ ታጥቢያለሽ፡፡
2. አንደኛ መውጣት ይፈልጋል፡፡ አያጠናም፡፡
3. እንግዶቹ በሙሉ ቦታቸውን ይዘዋል፡፡ፕሮግራሙን መጀመር ነው፡፡
4. ዝናብ እየዘነበ ነው፡፡ የእግር ኳስ ጨዋታው ቀጥሏል፡፡
5. ከተማዋ በቱሪስት ተጨናንቃለች፡፡ ነገ የደመራ በዓል በድምቀት ይከበራል፡፡
6. መጀመሪያ መሰላሉን አስደገፈ፡፡ በመስኮት ገባ፡፡

❖ ድርሰት

- **የድርሰት ምንነት**

ድርሰት የሚባለው ምናባዊ የፈጠራ ስራ ብቻ እንዳልሆነ ልብ ልንል ይገባል፡፡ በመሆኑም ድርሰት አንድን ነገር ምናባዊ ወይም ነባራዊ በሆነ መንገድ የምንገልፅበት የፁሁፍ ዘርፍ ነው፡፡ ምናባዊ ስንል አንድን መልዕክት ኪናዊ በሆነ መልኩ በአንባቢው አእምሮ ውስጥ ምስል ለመከሰት ሲባል የተመረጡ ቃላትን በመጠቀም የምናስተላልፍበት ስልት ሲሆን፣
ነባራዊ ስንል ደግሞ በገሀዱ ዓለም የሚታየውን ነገር እንዳለ ማቅረብ ማለት፡፡
ባጠቃላይ ድርሰት አንድ ፀሀፊ በአንድ ዓላማ ላይ ተመስርቶ የሚያየውን የሚያስበውንና የሚያውቀውን በፅሁፍ የሚገልፅበት ጥበብ ነው፡፡

አንድ ድርሰት ለመፃፍ ስንነሳ የመጀመሪያ ስራ መሆን ያለበት ርዕስ መምረጥ ነው።ርዕሱን ሲመረጥም ከግምት ሊያስገባቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ።

- የድርሰቱ ርዕስ ግልፅነት
- የድርሰቱ ርዕስ ወቅታዊነት
- ለፀሀፊው ችሎታ (እውቀት) መጣኝ መሆኑ
- መረጃ ለማግኘት አመቺ መሆኑ ናቸው።

ሁለተኛው ተግባር የተመረጠውን ርዕስ ማጥበብ ወይም መወሰን ነው። የድርሰት ርዕስ ያልተወሰነና ያልተገደበ ከሆነ የሀሳብ መንዛዛትና መዘበራረቅ ያስከትላል። ስለዚህ ርዕስ መጥበብና መወሰን ይኖርበታል። ቀጣዩ ስራ ከተለያዩ ምንጮች መረጃ መሰብሰብ ነው ይህም ከድምፅና ከፅሁፍ ሰነዶች እንዲሁም ሰውን በማነጋገር ሊሆን ይችላል። የሚገኙ መረጃዎችንም በየጊዜው እየመዘገብን መያዝ ይጠበቅብናል።

መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ ቀጣዩ ስራ አስተዋፅኦ መንደፍ ነው። አስተዋፅኦ በሚገባ ተሰራ ማለት የድርሰቱ ከፍተኛ ተግባር ተከናወነ ማለት ነው።

- **የአስተዋፅኦ ጥቅሞች**
  - ✓ ዓላማን ግልፅ ለማድረግና ሀሳብን ከዓላማ ጋር ለማዛመድ ያግዛል።
  - ✓ ድርሰቱ ከመፃፉ በፊት የሐሳቡን ቅንጅት ለማየትና ለማስተካከል ይጠቅማል
  - ✓ መልዕክትን ለማስተላለፍ ራሱን የቻለ መሳሪያ በመሆን ያገለግላል።
  - ✓ ፅሁፍ በሚፃፍበት ጊዜ ከዋናው ሀሳብ ላለማፈንገጥ ይረዳል

➢ የድርሰት አፃፃፍ

አንድ ድርሰት ለመፃፍ ስንነሳ የመጀመሪያ ስራ መሆን ያለበት ርዕስ መመረጥ ነው። ርዕስ ስንመርጥ ደግሞ በቂ መረጃ ልናገኝበት የምንችል መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል። ርዕስ ከመረጥን ቦኃላ ቀጣዩ ስራ ከተለያዩ ምንጮች መረጃ መሰብሰብ ነው። ይህም ከድምፅና ከፅሁፍ ሰነዶች እንዲሁም ሰውን በማነጋገር ሊሆን ይችላል። የሚገኙ መረጃዎችንም በየጊዜው እየመዘገብን መያዝ ይጠበቅብናል። መረጃ ከተሰበሰበ ቦኃላ ቀጣዩ ስራ አስተዋፅኦ መንደፍ ነው። አስተዋፅኦ በሚገባ ተሰራ ማለት የድርሰቱ ተግባር ተከናወነ ማለት። አስተዋፅኦ ከተዘጋጀ ቦኃላ ፣ ቀጣዩ በተያዘው ቅደም ተከተል መሰረት ድርሰቱን ወደ መፃፍ መግባት ነው። ድርሰት የተለያዩ ክፍሎች አሉት። እነርሱም መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ ናቸው።

- **መግቢያ**:- ስለ ድርሰቱ ፍንጭ የሚሰጥና የሚያስተዋውቅ፣ ድርሰቱ ያካተታቸውን ጉዳዮች በአጭሩ የሚገልፅ የድርሰቱ አካል ነው።
- **ሐተታ**:- በድርሰቱ ሊገለፅ የታሰበው ሐሳብ የሚገልፅበት ፣ በዝርዝር ሀሳቦች የተገነባ የድርሰቱ ዋና አካል ነው።
- **መደምደሚያ**:- የተገኘውን ውጤት የሚያሳይና የሐተታውን ፍሬ ነገር በአጭሩ የሚያቀርብ የድርሰቱ ክፍል ነው።

➢ የድርሰት ዓይነቶች

የድርሰት ዓይነቶች አራት ናቸው። እነሱም

1. ተራኪ ድርሰት
2. ገላጭ ድርሰት
3. ስዕላዊ ድርሰትና
4. አመዛዛኝ ድርሰት ናቸው።

1. ተራኪ ድርሰት

አንድን ነገር በትረካ መልክ እንዲህ ሆነ፤ ከዚያም እንዲህ ተፈጠረ እያለ የሚተርክ የድርሰት ዓይነት ነው። መሰረት የሚያደርገውም ባለፉ ጉዳዮች ላይ ነው። ታሪኩን የሚነግረንም እራሱ የድርጊቱ ተካፋይ ሊሆን ይችላል። አለበለዚያም ድርጊቱን የተመለከተ የደረሰበት በልምድ ያገኘው፤ ከሌላ ሰምቶ የሚያቀርበው ሊሆን ይችላል።

2. ገላጭ (አስረጅ) ድርሰት

የአንድን ነገር ምንነት፣ አገኛኘት፣ ባህሪያት፣ ዓይነት፣ መጠን፣ ቅርፅ አሰራር፣ ጠቀሜታ ጉዳት ወዘተ. የሚያብራራ የድርሰት ዓይነት ነው። አንድን ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ ነገር አስመልክቶ ምንድን ነው ምን ማለት ነው የተሰራው ከምንድን ነው እንዴት ተሰራ እንዴት እንደዚህ ሊሆን ቻለ ምን ጉዳት ወይም ጥቅም አለው ወዘተ. በሚል ለሚቀርቡ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ለመስጠት የሚሞክር ድርሰት ነው።

3. ስዕላዊ ድርሰት

ስዕላዊ ድርሰት የአንድን ነገር ምስልና ገፅታ በቃላት አማካይነት ስሎ ለማቅረብ የሚሞክር የድርሰት ዓይነት ነው። በዚህ የድርሰት ዓይነት ደራሲው የሚጠቀምባቸው ቃላት በሰው አእምሮ ውስጥ ምስል መፍጠር የሚችሉ መሆን አለባቸው። ይህ የድርሰት አፃፃፍ የአንድን ነገር ሁናቴ በዓይን እንዳዩት በፅጅ እንደዳሰሱት በጆሮ በቅርብ ሆነው እንደሰሙት በጠቅላላው ግዙፍ አድርጎ የሚያቀርብ የድርሰት ዓይነት ነው።

4. አመዛዛኝ ድርሰት

አመዛዛኝ ድርሰት አከራካሪ ስለሆኑ ጉዳዮች የሚፅፍ፣ አንባቢውን /አድማጩን/ የአንድን ጉዳይ እውነትነት ወይም ሐሰትነት ለማሳመን የሚጥር፣ ደራሲው /ፀሀፊው ለአንድ ወገን ቆሞ አንድን ጉዳይ በአንድ መልኩ ብቻ በመቃወም ወይም በመደገፍ ሊፅፍ የሚችልበት፣ ወይም ለሁለቱም አከራካሪ ሐሳቦች የቆሞ አንድን ጉዳይ በአንድ መልኩ ብቻ በመቃወም ወይም በመደገፍ ሊፃፍ የሚችልበት፣ ወይም

➢ ምሳሌያዊ አነጋገር

ምሳሌያዊ አነጋገር ከስነቃል ዘርፎች ውስጥ ሲሆን በቃልም ሆነ በፅሁፍ የሚተላለፍ መልዕክትን ውበትና ለዛ ያላብሳል፤ ሀሳብን እጥር ምጥን ባለ መልኩ ለመግለፅ ያገለግላል። ለዚህም ይመስላል አበው ‹‹ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ›› ያሉት።

የምሳሌያዊ አነጋገሮች ፋይዳ ከፍተኛ ነው። ለሀሳብ መቋጫ፣ ማጠናከሪያ፣ ማጉሊያና ግልፅ ማድረጊያ ይሆናሉ። ሰዎች በንግግራቸው ጣልቃ እያስገቡ ምሬታቸውን፣ ምኞታቸውን፣ ሀዘን

ደስታቸውን ይገልፀበታል፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ህብረተሰብን ያስተምራሉ፣ ይመክራሉ፣ ያስጠነቅቃሉ፣ ይገስፃሉ ወዘተ. ጥቂት ምሳሌዎችን እንመልከት፡-

- ✓ ባለፈ ጉዳይ ላይ መቆጨት አላስፈላጊ መሆኑን የሚመከረሩ
  - ○ ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራም
  - ○ የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም
  - ○ ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ
  - ○ ዝናብ ሲያባራ ወደ ዋሻ
- ✓ የመተባበርን ጠቀሜታ የሚገልፁ
  - ○ ከአንድ ብርቱ ሁለት መመድኃኒቱ
  - ○ አንድ አይወልድ አንድ አይፈርድ
  - ○ አንድ በሬ ስቦ አንድ ሰው አስቦ
  - ○ ድር ቢያብር አንበሳ ያስር
- ✓ ፈሪነትን የሚያወግዙ
  - ○ ፈሪ በገዛ ፀቡ ገላጋይ ይሆናል
  - ○ ፈሪና ንፋግ እያደር ይቆጨዋል
  - ○ ፈሪ ገአልጋ ወድቆ ይሞታል
- ✓ አለመናገር የሚጎዳ መሆኑን የሚያስተምሩ
  - ○ ካለመናገር ደጅአዝማችነት ይቀራል
  - ○ ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይደርስም
  - ○ ዝምታ ለበግም አልበጃት
  - ○ ዝምታ ከሞት ያስቆጥራል

መልመጃ ስድስት

የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሊነገሩ የሚችሉበትን ዐውድ ፈጥራችሁ ፃፉ፡፡

1. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
2. አንድ ቀን ቢስቱ ዓመት ይፀፀቱ
3. በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል
4. የቸኮለች አፍስሳ ለቀመች
5. አፍንጫን ሲመቱት ዓይን ያለቅሳል

➢ ቃላዊ ግጥም

ቃላዊ ግጥም የምንለው በአፈጣጠሩ የተናጠል ባለቤት የሌለውን፣ የህዝብ ሀብት ሆኖ ጠቅላላ ማህበረሰቡን በወል በማገልገል ከትውልድ ወደ ትውልድ የመሸጋገሪያ መንገዱ ቃላዊ ክዋኔ የሆነውን የስነ ቃል ዘርፍ ነው፡፡ ቃላዊ ግጥም የረዥም እድሜ ታሪክ አለው፡፡ መንስኤውም የሰው ልጅ የምርት ክንዋኔን ለማፋጠን ወይም በጎም ሆነ ክፉ ማህበረሰባዊ ገጠመኞችን ተሰሚነት ባለው መንገድ ለመሰሉ ለማስተላለፍ የነበረው ፍላጎት ነው፡፡ ይህ የሰው ልጅ ሀብት እንደ ምርት ክንዋኔዎች፣ እንደሰርግ፣ እንደለቅሶ፣ እንደክርስትና፣ ወዘተ. ባሉት አይረሴ ገጠመኞች የሚደረደሩ ወይም የሚዜሙ ግጥሞችን ያካትታል፡፡

- ➢ የቃላዊ ግጥም ማህበራዊ አጋጣሚዎች (አውዶች) በሰርግ፣ በክብረ በዓላት፣ በለቅሶ(ሙሾ)፣ በስራ ቦታዎች፣ በልጆች ጨዋታ፣ በጦርነት ወዘተ.
- ➢ የቃላዊ ግጥም ይዘቶች የፍቅር፣ የጥላቻ፣ የናፍቆት፣ የትዝታ፣ የብሶት፣ የንቀት፣ የሙገሳ ወዘተ.

ሽለላና ፉከራ የሚከወኑበት አጋጣሚና የሚከወኑበት ዓላማ አንድ ሆኖ በአቀራረባቸው ግን የየራሳቸው ባህሪ ያላቸው የቃላዊ ግጥም ዘርፍ ናቸው።
ብዙውን ጊዜ የሚከወኑት ማህበረሰቡን ለማነሳሳት የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ሲፈጠሩ ነው። በሚከወኑበት ጊዜ ከዋኙን እንዲሁም አድማጩን (ተመልካቹን) በስሜት በመሙላት አካሉና አእምሮው እንዲበረታና በሀሴት እንዲሞላ ከዚያ ልፎ በወኔ ንዲነሳና ለዓላማውም እንዲፀና ያደርጋሉ።
አከዋወናቸውን በተመለከተ ሽለላ በዜማ በባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ‹ክራር፣ ማሲንቆ፣ ዋሽንት) ታጅቦ የሚቀርብ ሲሆን ፉከራ ግን በቃል ንባብ መልክ የሚቀርብ ነው።
በሁለቱም ውስጥ ያሉ ቃላዊ ግጥሞች ይዘት ጀግናን፣ ደፋርን የሚያወድሱ፣ የሀገርን ፍቅርና ክብር የሚሰብኩ፣ ፈሪና ሰነፍን የሚኮንኑ ናቸው። ሽለላና ፉከራ ወኔ በመቀስቀስ ከፍተኛ ሚና ያላቸው ስነ ቃሎች ናቸው።

መልመጃ ሰባት

የሚከተሉትን የቃል ግጥሞች (የስራ፣ የፍቅር.... በማለት) በየወገናቸው መድቡ።

1. ይህን አያገዳይ ይህን እንጉርጉሮ
   ዓለም ያረጋል ሰው
   ከሀዘን ከትካዜ ከእዬዬ ሚብሰው
2. ወይ የኔ ጌታ ዋርካ ነህ ዋርካ
   ቢጠለሉብህ የማታስነካ
3. የበሮቹ ቁስ የበራው መምህር
   አቆላላፊ ክምር ለክምር
   ሐምሌ ነሐሴ ያልተራበ ሰው
   ሞፈር ቀንበሩን ቀሚስ ያልብሰው
4. እሷ ጠይም ልጅ ናት ጎፈሬዋ ጥቁር
   ከልቤ ገብታለች እንደ ግንደ ቆርቁር

➢ ሐረግ

✓ የሐረግ ምንነት

- ሐረግ ማለት ቃላት በስርኣት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት መዋቅር ነው።
- ከቃል ሰፋ ያለ መዋቅር ነው።

➢ የሀረግ ዓይነቶች

በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ የሀረጎች ዓይነት የሚወሰነው ለሀረጎች መሰረት ሆነው በሚገቡት ቃላት ነው። ከዚህ በላይ እንዳየናቸው የቃላት ክፍሎች ሁሉ ሀረጎችም በአምስት ይከፈላሉ።

እነሱም ፡-

- ✓ ስማዊ ሐረግ
- ✓ ግሳዊ ሐረግ
- ✓ ቅፅላዊ ሐረግ

- ✓ ተውሳከ ግሳዊ ሐረግና
- ✓ መስተዋድዳዊ ሐረግ ናቸው።

➢ **ስማዊ ሐረግ፡-** የሀረጉ መሪ ቃል ስም የሆነ የሐረግ ዓይነት ነው።
የሐረጉ መሪ ቃል በቀኝ በኩል ይገኛል።
ምሳሌ፡- የማር ጠጅ
የዶሮ ወጥ
የሸክላ ሳህን
ጠጅ ፣ ወጥ፣ ሳህን ፣ የሚሉት የሐረጉ መሪ ቃላት ስሞች በመሆናቸው ሐረጉን ስማዊ ሐረግ እንለዋለን።

➢ **ግሳዊ ሐረግ፡-** የሐረጉ መሪ ቃል ግስ የሆነ የሐረግ ዓይነት ነው። የሐረጉ መሪ ቃል በቀኝ በኩል ይገኛል።
ምሳሌ፡- ለበዓል በግ ገዛሁ።
ፈተናውን በጥሩ ሁኔታ አለፈ።
ገዛሁ፣ አለፈ የሚሉት ቃላት ግስ ናቸው። በመሆኑም የሀረጉ መሪ ቃል ግስ በመሆኑ ሀረጉ ግሳዊ ሐረግ ነው።

➢ **ቅፅላዊ ሐረግ፡-** የሐረጉ መሪ ቃል ቅፅል የሆነ የሐረግ ዓይነት ነው። በቅፅላዊ ሐረግ የሀረጉ መሪ ቃል የሚገኘው በቀኝ በኩል ነው።
ምሳሌ፡- ሁሉም ሰው እንደ ንብ ታታሪ መሆን አለበት።
ቶላ እንደ ወንድሙ ጎበዝ ተማሪ ነው።

➢ **ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ፡-** የሐረጉ መሪ ቃል ተውሳከ ግስ የሆነ የሐረግ ዓይነት ነው። የሐረጉ መሪ ቃል የሚገኘው በቀኝ በኩል ነው። ምሳሌ፡- ልጁ ክፉኛ ታመመ።
የእረፍት ሰዓት ገና ነው።

➢ **መስተዋድዳዊ ሐረግ፡-** ይህ ሐረግ ከሌሎቹ የሚለይበት ዋነኛ ባህሪው መሪው ቀኝ ወይም ግራ መሪ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል እንደ ሌሎች የሀረግ ዓይነት ከመሪው ብቻ ሐረግ ሊመሰረት አይችልም።

ምሳሌ፡- ከወንድሙ ጋር
በፍጥነት
መልመጃ ስምንት

በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ሐረጎች ምን ዓይነት ሐረግ እንደሆኑ ግለፁ።

1. በሀይሉ በጣም ቀይ ሹራብ ገዛ።
2. ቶለሳ እንዳ አባቱ ምንኛ ያሳዝናል።
3. ኢትዮጵያዊያን እንግዳ አቀባበል ያውቁበታል።
4. የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል።
5. እንደ እርግብ የዋህ ሁን።

6. የወርቅ አሮጌ የለውም፡፡
7. የአዋቂ ጠያቂ ልብ ያደርቃል፡፡
8. የወደቀው ልጅ ብዙ ደም ፈሰሰው፡፡
9. ስለሀገር ልማትና ደህንነት ማሰብ የዜጎች ሁሉ ሃላፊነት ነው፡፡
10. ተላላኪው የስብሰባውን ቃለ ጉባኤ አደለ፡፡

➢ የዓረፍተ ነገር ስልቶች

የዓረፍተ ነገር ስልት ማለት አንድ ዓረፍተ ነገር ከሚሰጠው አገልግሎት አንፃር በዓይነት የሚመደብበት ስልት ነው፡፡ በአማርኛ ለአራት ዓይነት አገልግሎት የሚውሉ የዓረፍተ ነገር ስልቶች አሉ፡፡ አነርሱም፡-

1. ሀተታዊ ዓረፍተ ነገር
2. ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር
3. ጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገር
4. አጋናኝ ዓረፍተ ነገር ናቸው፡፡

➢ ሀተታዊ ዓረፍተ ነገር

ሀተታዊ ዓረፍተ ነገር የአገላለፅ ስልቱ ሀተታዊ ቅርፅ ያለው ሲሆን አንድን ጉዳይ በተመለከተ ሀሳብ የሚያቀርብ ወይም አስተያት የሚሰጥ ነው፡፡ በዚህ የዓረፍተ ነገር ስልት የሚቀርበው ጉዳይ ከመነገር ባለፈ በጥያቄ መልክ ወይም በተጋነነ ሁኔታ አይቀርብም፡፡ ይህ ዓረፍተ ነገር በአሉታዊ ወይም በአዎንታዊ መልክ ሊነገር ይችላል፡፡ ዓረፍተ ነገሩ የያዘው ሀሳብ አፍራሽ ከሆነ አሉታዊ ዓረፍተ ነገር ሲባል፣ በአዎንታ ከተነገረ ደግሞ አዎንታዊ ዓረፍተ ነገር ይባላል፡፡

ምሳሌ፡-

1. ለአዲሱ ቤት አዳዲስ እቃዎች ገዛ፡፡
2. ጫልቱ ጎበዝ ተማሪ በመሆኗ ተሸለመች፡፡
3. ዛሬ ትምህርት ቤት አልሄድም፡፡

በምሳሌዎቹ የቀረቡት ዓረፍ ነገሮች ሀተታ ናቸው፡፡ ተግባራቸው የተደረገን /የሆነን/ ድርጊት መግለፅ፣ መናገር ነው፡፡

➢ ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር

በትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር የተላለፈው ሀሳብ በውስጡ ትዕዛዝን ያዘለ ነው፡፡ ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር ከተነገረ በኋላ መልዕክቱ የተላለፈበት ሌላው ወገን ምላሽ እንዲሰጥ ጫና የሚፈጥር ድምፀት ያለው የዓረፍተ ነገር ስልት ነው፡፡

ምሳሌ፡-

1. የመኪናህን ፍጥነት ቀንስ፡፡
2. የበላህበትን ሳህን እጠብ፡፡
3. የወሰድከውን ገንዘብ መልስ፡፡

በምሳሌው የቀረቡት ሶስት ዓረፍ ነገሮች አንድ አካል ለሌላ አንድ አካል አንድ ድርጊት እንዲፈፅም በጫና በትዕዛዝ፣ መልዕክት የሚያስተላልፍ ናቸው።

➢ ጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገር

ጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገር የአገላለፅ ስልቱ በጥያቄ መልክ የሚቀርብ ነው። አንድ ሀሳብ በጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገር ተነግሮ ለሌላ ወገን ሊተላለፍ ይችላል። ከስያሜው እንደምንረዳውም በጥያቄ ላይ ተመስርቶ የሚዋቀር ነው።

ምሳሌ፡-

1. ልጆቻችን ባህላቸውን እንዳይረሱ ምን ማድረግ አለብን
2. አውሮፕላኑ በስንት ሰዓት እንደሚገባ ማንን ልጠይቅ
3. ሲኮርጅ የተያዘው ተማሪ ምን ዓይነት ቅጣት ይቀጣ

➢ አጋናኝ ዓረፍተ ነገር

አጋናኝ ዓረፍተ ነገር ስልቱ ሀሳብን በማጋነን መልክ የሚያቀርብ ነው። ይህ የዓረፍተ ነገር ስልት እንደሌሎቹ ሁሉ ተግባሩ ሀሳብ መግለፅ ቢሆንም ሲቀርብ ግን የተደረገውን ድርጊት ከተራ አገላለፅ ባለፈ አክብዶና አጋንኖ የሚያሳይ ነው።

ምሳሌ፡-

1. አቤት! አንበሲት! ሴት ማለት እሷ ናት! መብቷን አስከበረች።
2. እሰይ! እናቴ መጣች።

መልመጃ ዘጠኝ

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በስልታቸው መድቡ

1. ተማሪው ደብተሩን ቀደደው።
2. ሠራተኛው የፋብሪካውን ምርት ያሳድግ።
3. አጥፊው ተለይቶ እስኪታወቅ ሁሉንም ይዛችሁ እሰሩ።
4. ወ/ሪት ጫላቱ ለውድድር የምትቀርበው መቼ ነው?
5. አብዲ ከሄደበት አልተመለሰም።
6. አቤት አበላል! አቤት አጎራረስ! ያን ሁሉ ምግብ ለመጨረስ ደቂቃም አልፈጀበት።

➢ ፈሊጣዊ አነጋገር

ፈሊጥ እያንዳንዱ ቃል በተናጠል ከሚሰጠው የተለየ ፍች የሚያስገኝበት የቃላት ቅንጅት ነው። አብዛኛው ጊዜ የተለያዩ ቃላት እርስ በርስ በሚቀናጁበት ጊዜ ፈሊጥን ሲፈጥሩ ትርጉማቸው ከወትሮው ይለያል። ይህን አስመልክተው እነ አምሳሉ አክሊሉ ሲገልፁ፣ ፈሊጥ በቃላት ልዩ ልዩ ዘዴ የመጠቀም አንደኛው መንገድ እንደመሆኑ ባጠቃላይ ይዘቱ እያንዳንዱ ከሌሎች ቃላት ጋር በሚቀናጅበት ጊዜ በመሰረቱ ከነበራቸው ፍች የተለየ ፍች የሚሰጡበት ሁናቴ ሲሆን በዝርዝር ይዘታቸው ደግሞ ቃላት መጀመሪያ ለቆሙለት እሳቤ ተመሳሳይ ለሆኑ ሌሎች እሳቤዎች በመዋል ትርጉማቸው እየሰፋ የሚያድግበት ዘዴ ነው።

የአማርኛ ፈሊጦች ባህሪ

ፈሊጦች ከሌሎች ቃላት የሚለዩባቸው ባህሪያት አሏቸው፡፡ እነሱም፡-

- ✓ ከጥንድ ቃላት በትርጉማቸው ይለያሉ፡፡
- ✓ አብዛኛውን ጊዜ ከአንዱ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ በቀጥታ አይተረጎሙም፡፡
- ✓ አንዳንድ ጊዜ የተለመደውን የሰዋስው ስርዓት ይጥሳሉ፡፡
- ✓ ከቃላት ቀጥተኛ ትርጉም ተነስቶ ፍች ለመስጠት ይከብዳል፡፡
- ✓ ከሌሎች ቃላት በተለየ መልኩ ሀሳብን አጠናክረው የመግለፅ ሀይል ላቸው፡፡

ስለዚህ የአማርኛ ፈሊጦች ለንግግራችን ለዛ፣ ለፅሁፋችን ደግሞ አፅንኦት በመስጠት ያገለግላሉ፡፡
የተወሰኑ ፈሊጦችን በምሳሌነት እንደሚከተለው እንመልከት

ፈሊጥ	ትርጉም
1. ዓይነ ልም	ተንኮለኛ
2. ነፍስ አወቀ	አደገ
3. ሁለት ልብ	ወላዋይ
4. ልበ ሰፊ	ቻይ፣ ታጋሽ
5. አንጀቱ ራሰ	የልቤ ደረሰ
6. የግንባር ስጋ	የማይደብቁት ነገር
7. እጁን ከብብቱ አገባ	ፈፅሞ ሰነፈ
8. ወገበ ቀላል	ፈጣን
9. ለጆሮ ብሎ	ለዝና ብሎ
10.የአዞ እንባ	የውሸት ሀዘን

መልመጃ አስር

ለሚከተሉት ፈሊጦች ትርጉማቸውን ስጡ

1. እጁን ጫነበት
2. ልቡ ቀረ
3. አንገት ለአንገት
4. አፉን አዳጠው
5. ወገቡን ያዘ
6. ጆሮ ሰጠኝ
7. ጥራዝ ነጠቅ
8. ገመና ከታች
9. ሆድና ጀርባ
10. አንደበተ ርቱዕ

➢ ቅኔ

ቅኔ ሊተላለፍ የተፈለገን ዋና መልዕክት በሌላ ሃሳብ ሸፍኖ የማቅረብ ስልት ነው፡፡ በውስጡ ሰምና ወርቅ በመባል የሚታወቁ መልእክቶችን ይይዛላ፡፡

ቅኔ ሲመሰረትም ቀጥተኛውን እና ምስጢራዊውን መልዕክት ባንድ አዋህዶ የሚይዝ ቃል ወይም ሀረግ በገለባው ውስት የሚኖር ሲሆን እሱም ህብረ ቃል ይባላል፡፡ ይህ ህብረ ቃልም ሁለት ነገሮችን አጣምሮ ይይዛል፡፡ እነሱም ሰም እና ወርቅ ናቸው፡፡ ህብረ ቃል በግጥሙ መጀመሪያ፣ መካከልና መጨረሻ ሊገኝ የሚችል ቢሆንም አባዛኛውን ጊዜ የሚገኘው ግን በስተመዳረሻ ነው፡፡

ሰም ቅኔው ለማስተላለፍ የፈለገውን ምስጢራዊ መልዕክት እንደ መሸፈኛ ወይም መጋረጃ የሚጠቀምበት እና ቅኔውን በመጀመሪያ ስናስብ ቶሎ ወደ አእምሮአችን የሚመጣ ነው።

ወርቅ የሚባለው ደግሞ ብዙ በማሰላሰልና በመመራመር የሚገኘው መልዕክት ነው።

የቅኔን ሰምና ወርቅ ለመለየት የሚያገለግሉ ብዙ ዘዴዎች አሉ። ከእነሱም ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሱት የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ቃልን ከቃል በማቀላቀል በህብረ ቃሉ ውስጥ ተከታትለው የሚገቡ ቃላትን በማገናኘት ሌላ ቃል ወይም ሀረግ መፍጠር፣

ምሳሌ፡ 1 እኛ አገር ተቀምጦ በክርስቲያን ስም
አሳ ማን ይበላል በሁዳዴ ፆም
ህብረቃል፡- አሳ ማን
ሰም፡- በሁዳዴ ፆም አሳ አይበላል።
ወርቅ፡- በሁዳዴ ፆም አሳማ ይበላል

ለ. በቃል ውስጥ የሚገኙ ሆሄያትን በመከፈፈል ፣ በህብረቃልነት የተያዘውን ቃል በመሰንጠቅ ሁለት አዲስ ትርጉም ያላቸው ቃላትን መፍጠር፣

ምሳሌ 2. የለመንኩሽ ብዕር ስለጠፋብሽ
እሰይ ደስ ብሎኛል ባልተገኘልሽ
ህብረ ቃል፡- ባላተገኘልሽ
ሰም፡- ጠፍቶ በቀረ
ወርቅ፡- የትዳር ጓደኛ ተገኘልሽ

ሐ. ከቃላት መካከል የተወሰኑ ሆሄያት ከፊት ካለው ወስዶ በተከታይ ወዳለው ወይም ከተከታዩ ወስዶ ፊት ወዳለውበመደረብ አዲስ ቃል እንዲሆን በማድረግ፣

ምሳሌ፡ 3. አዳራሹ ሰፊ በሩ አልጠበባችሁ
በተራ በተራ ምነው መግባታችሁ
ህብረ ቃል ፡- በተራ በተራ
ሰም፡- ተራን ጠብቆ መግባት ለምን አስፈለገ
ወርቅ፡- ረሀብተኛ በሆኑ ሰዎች ተራ ለምን ገባችሁ፡፤

መ. ህብረ ቃሉን አጥብቆና አላልቶ በማለት (በማንበብ)፣

ምሳሌ፡4. ማድጋውን ሁሉ ታስቆጥራላችሁ
አለቃችሁ እንጂ ማን ወሰደባችሁ
ህብረ ቃል፡- አለቃችሁ
ሰም፡- እቃችሁ አለ። አልተሰረቀም
ወርቅ፡- ተጨርሳችኋል ፣ አልቃችኋል
ሀላፊያችሁ ነው የወሰደባችሁ

ሠ. ከአንድ በላይ ፍች ያላቸውን ቃላት ሁለት ትርጉማቸውን በማጤን፣

ምሳሌ፣ 5. ላረቂውም ኮራሽ፣ ለውስኪውም ኮራሽ፣ አንቺ ግድ የለሽም
የወደድሽው ጠላ አልተገኘልሽም

ህብረ ቃል፡- ጠላ
ሰም፡- የሚጠጣ ጠላ ብትፈልጊም አልተገኘም
ወርቅ፡- አንቺ የወደድሽው ሰው ስለጠላሽ(ሽላዳዳስ) አልተገኘም
ረ. የቃላት እማሬያዊና ፉካሬያዊ ፍችን በማጤን
ምሳሌ፡ 6. ብሄድ በወለጋ ብሄድ በጎጃም
እንዳንቺ ዓይነት በቅሎ አይቼ አላውቅም
ህብረቃል፡- በቅሎ
ሰም፡- እንዳንቺ አይነት ቆንጆ አላየሁም
ወርቅ፡- እንዳንቺ ዓይነት የማትወልጅ(መካን) አላየሁም

መልመጃ አስራ አንድ

ከላይ የቀረበውን የቅኔ ፅንሰ ሀሳብ እና ምሳሌዎች በጥሞና አንብባችሁ ከተረዳችሁ በኋላ ቀጥሎ የቀረቡትን ቅኔዎች ህብረ ቃል፣ ሰምና ወርቁን ለይታችሁ አሳዩ፡፡

1. አፍር መልሱ እንጂ ድንጋይ ለምናችሁ፣
   የቀለም ቀንድ ነው ትሰብሩታላች፡፡
2. ማነው ይህን መፅሀፍ ሳያትም የቀረ ፣
   መምህሩስ የሚሉት አትሙት ነበረ፡፡
3. በባላገር ነበር ኑሮስ የሚሻል፣
   ከተማ ሰው ገብቶ ምን ሰው ይሆና፡፡፡
4. እኔም በልቼ አልጠገብኩ፣
   እንደው አ ብዬ ቀረሁ፡፡

5. ሁል ጊዜ ፀጉርሽን ከምትቆነጂ፣
   ለእኔም ባርኔጣ አለኝ አንቺም በሻሽ ሂጂ፡፡

➢ ጅምር ምሳሌያዊ አነጋገር ማሟላት

ስለምሳሌያዊ አነጋገር ከዚህ ቀደም የተሰጠውን ማስታወሻ መመልከት ትችላላችሁ፡፡

መልመጃ አስራ ሁለት

ከዚህ በታች የቀረቡትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ፡፡

1. አለባብሰው ቢያርሱ ----------::
2. አህያ ለአህያ ቢራገጥ ----------::
3. አንበሳ ሲያረጅ ----------::
4. ከበሮ በሰው እጅ ያምር ----------::
5. እባብ ያየ ----------::
6. አሳን መብላት ----------::
7. ---------- እጅ ያስመጥጥ፡፡
8. ---------- ለባልዋ ዘውድ ናት፡፡
9. ---------- ያላት አይጥ አትሞትም፡፡
10. ---------- ዳቦ ይልሳል፡፡

➢ ደብዳቤ

ደብዳቤ እንደይዘቱና ዓላማው ዓይነቱ በርካታ ቢሆንም በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊጠቃለል ይችላል። ይኸውም ፡-

- ✓ የመስሪያ ቤት ደብዳቤ
- ✓ የወዳጅ ዘመድ (የግል ደብዳቤ) ናቸው።

- የወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ የምንለው ፍቅረኛሞች ፣ ቤተሰቦች፣ ወዳጅ ዘመዶች እርስ በርስ የሚፃፃትን ደብዳቤ ነው፡

- የመስሪያ ቤት ደብዳቤ የምንለው በስራ ዓለም ውስጥ ስራ ነክ ጉዳዮችን ለመፈፀምና ለማስፈፀም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ግለሰቦችና፣ መስሪያ ቤቶች በተጨማሪ ድርጅቶች እርስ በርስ የሚለዋወጡትን ደብዳቤ ነው። በዚህ የደብዳቤ ዓይነት መስሪያ ቤት ለመስሪያ ቤት፣ መስሪያ ቤት ለግለሰብ፣እንዲሁም ግለሰብ ለመስሪያ ቤት ሊፅፍ ይችላል።
  የስራ ደብዳቤዎች በዋናነት በሁለት ይከፈላሉ። እነርሱም የድርጅት ወይም የመ/ቤት የስራ ደብዳቤ እና የግል የስራ ደብዳቤ የሚባሉት ናቸው።
  የንግድ ስራ ደብዳቤ ከድርጅት ወይም ከመ/ቤት የስራ ደብዳቤ የሚመደብ ሲሆን አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት የንግድ ስራን (ሽያጭን፣ ግዢን ወይም ልውውጥን) አስመልክቶ ለሌላ ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚፃፍ ደብዳቤ ነው። ይህ ዓይነቱ ደብዳቤ የዕቃዎችን ዋጋ ለመጠየቅ፣ የዋጋ መጠየቂያ ደብዳቤ ምላሽ ለመስጠት ስሞታ ካለ ለመሰንዘር፣ ለቀረበው የግዢ ጥያቄ ፈጣንና አርኪ ምላሽ ከተገኘ ምስጋና ለማቅረብ ወዘተ. የሚፃፍ ነው።

የስራ ደብዳቤ ቅርፅ የሚከተለውን ይመስላል

የራስጌ ማህተም

ቁጥር _____
ቀን _____

ለ _____
ከተማ
ጉዳዩ፡- _____
_____
_____
_____
_____
_____ ::
ከሰላምታ ጋር!

የግርጌ ማህተም
ግልባጭ፡- _____

ፊርማ
ሙሉ ስም(ሀላፊነት)

መመሪያ፡ ከዚህ ቀጥሎ በዚህ ጥራዝ ውስጥ ከተጠቀሱት ይዘቶች የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል ጥያቄዎቹን በጥሞና በማንበብ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ።

1. ‹‹እውነተኛ›› በሚለው ቃል ውስጥ ቃል መስራቹ ቅጥያ የትኛው ነው?
   ሀ. -ተኛ ለ. -ነት ሐ. -ኛኛ መ. -ነተኛ
2. ‹‹አስገረፋት›› በሚለው ቃል ውስጥ መድረሻ ላይ ያለችው ቅጣይ ምዕላድ /-ት/ ---------- ትገልፃለች።
   ሀ. ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አንስታይ ፆታን
   ለ. ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አንስታይ ፆታን
   ሐ. ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕታይ ፆታን
   መ. ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕታይ ፆታን
3. ‹‹ደኖቻችን›› በሚለው ቃል ውስጥ ያሉት ቅጣይ ምዕላዶች ከይዘት አንፃር ---------- ያመለክታሉ።
   ሀ. ብዛትና ግብርን ሐ. ዓይነትና መጠንን
   ለ. ብዛትና ባለገንዘብነትን መ. ድርጊትንና ጉዳይን
4. ከሚከተሉት መካከል አንዱ ለምስርት ቃል ምሳሌ አይደለም።
   ሀ. ወታደሩን ለ. ጉልበተኛ ሐ. ሰውነት መ. ብልግና
5. ከሚከተሉት መካከል አንዱ ጥገኛ ምዕላዶችን በውስጡ የያዘ ቃል ነው።
   ሀ. መሃረብ ለ. ወረቀት ሐ. ምራቅ መ. ምርቃት
6. ---------- በመነሻውና በመድረሻው ላይ ቅጣይ ምዕላዶች የሌሉት ቃል ነው።
   ሀ. አውራሪስ ለ. አይበላም ሐ. አልመጣም መ. አስተባበረ
7. ‹‹ተባበሩባቸው›› በሚለው ቃል ውስት የመተባበርን ተግባር የፈፀሙት እነሱ መሆናቸውን የሚያመለክተው ቅጣይ ምዕላድ የትኛው ነው?
   ሀ. /-አቸው/ ለ. /-ቸ/ ሐ. /-ባቸው/ መ. /-ኡ/
8. ‹‹ምንዱባን›› በሚለው ቃል ውስጥ የብዙ ቁጥር አመልካች ቅጣይ ምዕላድ የትኛው ነው?
   ሀ. /-አን/ ለ. /-ን/ ሐ. /-ባን/ መ. /-ኡ/
9. ከሚከተሉት ቃላት መካከል አንዱ /-አም/ን መድረሻው ላይ መቀጠል ይችላል።
   ሀ. መልክ ለ. ቁማር ሐ. ነገር መ. አመል
10. ‹‹ፀሀፊያን›› በሚለው ቃል ውስጥ የብዜት አመልካች ሆኖ የገባው የትኛው ቅጥያ ነው?
    ሀ. -ያን ለ. -ያ ሐ. -ኣን መ. -ን
11. ከሚከተሉት ውስጥ ለነፃ ምዕላድ ምሳሌ የሚሆነው የትኛው ነው?
    ሀ. ቤት ለ. ቤቱ ሐ. ቤታችን መ. ቤቶች
12. ‹‹በግ›› ምዕላድም ቃልም ነው እንዲባል ያስቻለው ምንድን ነው?
    ሀ. ከእሱ ወዳነሱ አሃዶች ሊከፈል የማይችል መሆኑ ሐ. ፍች ያለው አሃድ መሆኑ
    ለ. በቃልነቱ ባንዱ የቃል ክፍል የሚመደብ መሆኑ መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ
13. ከቃላቱ ውስጥ መድረሻ ቅጥያ ያለው የትኛው ነው?
    ሀ. ፍትህ ለ. ሰብኣዊ ሐ. ሃገር መ. እንቅልፍ

14.ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ አንዱ ነፃ ምዕላድ ነው።
ሀ. መሸጋገሪያ ለ. መጥረጊያ ሐ. ብርጭቆ መ. መዘፍዘፊያ
15.‹‹በመቅደላ አምባ ብዙ ነዋሪዎች አሉ። ሰፈራቸውም እንደዓይነታቸው የተለያየ ነው።›› በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ያለው -ኣቸው ተግባሩ ምንድን ነው?
ሀ. ዖታን ማመልከት ሐ. ንብረትን ማመልከት
ለ. ቁጥርን ማመልከት መ. ባለቤትን ማመልከት
16.‹‹ለጉንጮችሽ›› በሚለው ቃል ውስጥ ዖታን ለማመልከት የገባው ጥገኛ ምዕላድ ምንድን ነው?
ሀ. -ችሽ ለ. -ሽ ሐ. -ኦችሽ መ. -ች
17.ከሚከተሉት ውስጥ የእርባታ ምዕላድ ያለው ቃል የትኛው ነው?
ሀ. ተወዳጅነቷ ለ. ፖለቲካዊ ሐ. ዝናባማነት መ. ግብራዊ
18.‹‹አስተዋዋቂው ወደ መድረክ አመራ።›› በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ የተሰመረበት ሐረግ ለብቻው ቢነገር ዓይነትቱ ምንድን ነው?
ሀ. መስተዋድዳዊ ሐረግ ሐ. ስማዊ ሐረግ
ለ. ግሳዊ ሐረግ መ. ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ
19.ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ የሆነው የቱ ነው?
ሀ. እጅግ ብርቱ ጀግና ሐ. ከጓደኛው የባሰ ተንኮለኛ
ለ. ከእናቱ ጋር ቶሎ መ. እንደኔ እልኸኛ
20.የእኔና የመልካሙ ጓደኝነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ ነው።
በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ያለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ---------- ነው
ሀ. የእኔና የመልካሙ ጓደኝነት ሐ. ከጊዜ ወደ ጊዜ
ለ. እያደገ የመጣ ነው መ. ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ
21.‹‹ሰውየው ከባሌ እስከ አዲስ አበባ በእግሩ መጣ።›› በሚለውዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ምንድን ነው? ሀ. ስማዊ ሀረግ ለ. ቅፅል ሐ. መስተዋድዳዊ ሀረግ መ. ነፃ ምዕላድ
22.ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ቅፅላዊ ሀረግ ያለበት ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው?
ሀ. አሁን በጣም ስለደከመኝ መተኛት እፈልጋለሁ።
ለ. በርትቶ ያጠና ተማሪ ውጤት ያመጣል።
ሐ. ትላንት የገዛሁት መፅሀፍ መኪና ውስጥ ጠፋብኝ።
መ. በጣም ፀሀያማ ቀን ስለሆነ ጃኬት አትልበስ።
23.ያ በጣም ጎበዙ የክፍላችን አለቃ በከፍተኛ ውጤት ተመረቀ።
በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ግሳዊ ሀረጉ የትኛው ነው?
ሀ. ያ በጣም ጎበዙ የክፍላችን አለቃ ሐ. የክፍላችን አለቃ በከፍተኛ ውጤት
ለ. በከፍተኛ ውጤት ተመረቀ መ. ጎበዙ የክፍላችን አለቃ በከፍተኛ
24.ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ስማዊ ሀረግ ያልሆነው የትኛው ነው?
ሀ. ወንድሜ የገዛት መኪና ሐ. እንደወንድሙ በጣም ቀልጣፋ
ለ. ከስራ የተሰናበቱት የመስሪያ ቤቱ ኃላፊ መ. የልጅቷ ማራኪ አነጋገር
25.ከሚከተሉት ሀረጎች ውስጥ ለስማዊ ሀረግ የትኛው በምሳሌነት ያገለግላል?
ሀ. ወደ ቤቱ ሊሄድ ሲል ሐ. በድንገት ቤቱ ፈረሰ
ለ. የአበበ እናት ቤት መ. ቤቱን ገዛች

26. ትፍስህት ከጠንካራ ሴት የዩንቨርሲቲ ተማሪዎች መካከል በአብነት ትጠቀሳለች፡፡ የተሰመረበት ቃል ለየትኛው የሀረግ ዓይነት ምሳሌ ይሆናል?
ሀ. ለቅፅላዊ ሀረግ ሐ. ለስማዊ ሀረግ
ለ. ለግሳዊ ሀረግ መ. ለመስተዋድዳዊ ሀረግ

27. ‹‹ጋቢው ተቀደደ፡፡›› የሚለው ተራ ዓረፍተ ነገር ወደ ስማዊ ሀረግ ቢለወጥ የትኛው ትክክል ይሆናል?
ሀ. ጋቢው ይቀደድ ሐ. ቀዳዳ ጋቢ
ለ. ጋቢው ተቀደደ እንዴ መ. ጋቢው ሊቀደድ ነው

28. ከሀረጎቹ መካከል ቅፅላዊ ሀረግ የሆነው የትኛው ነው?
ሀ. በጣም ዘገምተኛ ሐ. ጠመዝማዛው መንገድ
ለ. ቀዩ ልጅ መ. ብሄራዊ ፈተና

29. ‹‹በክብት እርባታ የሚተዳደር ገበሬ አርብቶ አደር ተብሎ ይጠራል፡፡›› በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ግሳዊ ሀረጉ --------- ነው፡፡
ሀ. በክብት እርባታ ሐ. የሚተዳደር ገበሬ
ለ. አርብቶ አደር ተብሎ ይጠራል፡፡ መ. ገበሬ አርብቶ አደር ተብሎ

30. ‹‹በጣም ግዙፍ ሰውነት ያላቸው ሰዎች ሩጫ ይከብዳቸዋል፡፡›› በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት --------- ነው፡፡
ሀ. የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት ሐ. ስማዊ ሀረግ
ለ. ቅፅላዊ ሀረግ መ. መስተዋድዳዊ ሀረግ

31. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በአሉታ የቀረበ መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው?
ሀ. ፈተናው ምን ያህል ይከብዳል? ሐ. ጓደኛህ ከሆስፒታል አልወጣም?
ለ. መፃህፍት ቤቱ ተዘጋ እንዴ ? መ. ወንድምህ መቼ ይመለሳል?

32. ‹‹አጥፊው ተለይቶ እስኪታወቅ ሁሉንም ይዞ አሰራቸው፡፡›› የሚለው አወንታዊ ዓረፍተ ነገር ወደ አሉታዊ ዓረፍተ ነገር ሲለወጥ ምን ይሆናል?
ሀ. አጥፊው ተለይቶ እስኪታወቅ ሁሉንም ይዞ አይሰራቸው፡፡
ለ. አጥፊው ተለይቶ እስኪታወቅ ሁሉንም ይዞ እንዳያስራቸው፡፡
ሐ. አጥፊው ተለይቶ እስኪታወቅ ሁሉንም ይዞ አላሰራቸውም፡፡
መ. አጥፊው ተለይቶ እስኪታወቅ ሁሉንም ይዞ አይሰር፡፡

33. ለመጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር የትኛው በይበልጥ ምሳሌ ይሆናል?
ሀ. ዝማም ወደ ሱፐርማርኬት መሄድን ታዘወትራለች
ለ. ያንቱ እየገሰገሰች የሄደችበት ምክንያት አልታወቀም
ሐ. ሰይፈ በዓመቱ ለመስራት ያሰበውን መቼ ያሳካል
መ. ጀማል መፅሀፍ ለመድረስ ደፋ ቀና ይላል

34. ለአሉታዊ ዓረፍተ ነገር በምሳሌነት የትኛው ሊጠቀስ ይችላል?
ሀ. ጥያቄዎችን በተለያየ መንገድ መፃፍ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡
ለ. ጥያቄዎችን በተለያየ መንገድ ለመፃፍ ዝግጅት ያስፈልጋል፡፡
ሐ. ጥያቄዎችን በተለያየ መንገድ መፃፍ ይቻላል፡፡
መ. ጥያቄዎችን በተለያየ መንገድ መፃፍ አይከብድም፡፡

35. እኔ ሳውቅ አቶ መኮንን በልጅነታቸው የወለዱት ልጅ ነበራቸው፡፡
ይህንን ዓረፍተ ነገር ወደ አሉታዊ ዓረፍተ ነገር ለመለወጥ በተሰመረበት ቃል ላይ ሊቀጠል የሚገባው የትኛው ነው?
ሀ. አል .... ም ለ. ያል ... ን ሐ. አል ... ን መ. አይ ... ም

36. ከተከታዮቹ ዓረፍተ ነገሮች መካከል በአወንታዊ ስልት የቀረበው የትኛው ነው?
ሀ. ለእህቴ ውሻውን እንድታስረው ነግሬያታለሁ፡፡
ለ. ጫጫታ በበዛበት ቦታ መዝናናት አልወድም፡፡
ሐ. የምፈልገው ሽቶ ከሱቁ አለመኖሩ ተነገረኝ፡፡
መ. ስለረፈደብኝ ፀጉሬን ሳላበጥር ከቤት ወጣሁ፡፡

37. ግጥም ከዝርው ፅሁፍ ከሚለይባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች መካከል ዋነኛው ምንድን ነው?
ሀ. የዘይቤ አጠቃቀሙ ሐ. የቃላት ምርጫ
ለ. የስንኝ አጠቃቀም መ. የጠበቀ ምት

38. ድርሰት ሲፃፍ አስተዋፅኦ መንደፍ ለምን ይጠቅማል?
ሀ. የፅሁፍን ሀሳብ አሳጥሮ ለማቅረብ ሐ. መረጃን በየፈርጁ ለማቅረብ
ለ. በጥቂት ቃላት ብዙ ሀሳብ ለመግለፅ መ. ስለርዕሱ ትንታኔ ሰጥቶ ለመፃፍ

39. ከሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች መካከል አመዛዛኝ ድርሰትን ለመፃፍ አመቺ የሆነው የትኛው ነው?
ሀ. የወጣቶች ንቁ ተሳትፎ ለሀገር ልማት እንደሚጠቅም ተገለፀ፡፡
ለ. ቴክኖሎጂን በመቀበል ረገድ ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ፈጣን ናቸው፡፡
ሐ. የዘንድሮው የዘመን መለወጫ በዓል በድምቀት ተከበረ፡፡
መ. ትምህርት ለሀገር ብልፅግና አስተዋፅኦ እንዳለው ምሁራን ይገልፃሉ፡፡

40. በዛሬው ዕለት የሚሰጠውን የአጠቃላይ ትምህርት ፈተና ለማሰራጨት፣ ለማስፈተንና ለመፈተን በየትምህርት ቤቱ የሚታየውን ሽርጉድ በተመለከተ ለአንባቢ ለማስቃኘት በየትኛው የድርሰት ዓይነት መፃፍ የተሻለ ነው?
ሀ. በአመዛዛኝ ሐ. በተራኪ ለ. በገላጭ መ. በስዕላዊ

41. ግጥም ከዝርው ፅሁፍ በምን ይለያል?
ሀ. በዘይቤ በመጠቀሙ ሐ. በዓረፍተ ነገር በመፃፉ
ለ. በሙዚቃዊ ቃናው መ. ነገሮችን ዘርዘር አድርጎ በመግለፁ

42. ምስል ከሳች ቃላትን በሰፊው የምንጠቀመው በየትኛው የድርሰት ዓይነት ነው?
ሀ. በተራኪ ለ. በስዕላዊ ሐ. በአመዛዛኝ መ. በገላጭ

43. አንድን ጉዳይ በበቂ ማስረጃዎችና መረጃዎች የሚያብራራ የድርሰት ዓይነት ---------- ነው፡፡
ሀ. ገላጭ ለ. ተራኪ ሐ. አመዛዛኝ መ. ስዕላዊ

44. ከዚህ በታች የቀረበው አንቀፅ ለየትኛው የድርሰት ዓይነት ምሳሌ ሊሆን ይችላል?
‹‹ሰፈሩ ታምሷል፡፡ ድብልቅልቅ ያለ ጩኸት ይሰማል፡፡ የግቢው በር በኃይል ተንኳኳ፡፡ እህቴ እመር ብላ ወደ ውጭ ወጣች፡፡ ጥይት ተተኮሰ፡፡ በርሬ ወጣሁ፡፡ ግራ እጇ ክፉኛ ተጎድቷል፡፡ ፊቷ በደም ተጨማልቋል፡፡ አንገቷ ላይ ተጠመጠምኩ፡፡ መብራቱ በድንገት እልም አለ፡፡ ድቅድቅ ጨለማ ዋጠን፡፡››
ሀ. ለተራኪ ለ. ለገላጭ ሐ. ለስዕላዊ መ. ለአመዛዛኝ

45. አንድ ፀሀፊ የአንድን ጉዳይ እውነትነት ወይም ሀሰትነት በማስረጃ እያስደገፈ ለማሳመን የሚጥርበት የድርሰት ዓይነት ምን በመባል ይታወቃል?
ሀ. ተራኪ ድርሰት ለ. አስረጅ ድርሰት ሐ. ስዕላዊ ድርሰት መ. አመዛዛኝ ድርሰት

46. አንድን ፅሁፍ ስንፅፍ አስቀድመን አስተዋጽኦ (ቢጋር) ማዘጋጀት ያለብን ለምንድን ነው?
ሀ. ቃላትን ባግባቡ ለመምረጥ
ለ. የጽሁፋችንን መልዕክት ለአንባቢው ግልፅ ለማድረግ
ሐ. የጽሁፍ ማስፋፊያ ዘዴዎችን ለመወሰን
መ. ከምንፅፈው ጽሁፍ ዋና ሀሳብ ላለማፈንገጥ

47. ቀኑን ሙሉ እንባ ሲወርድበት የዋለው ፊቱ ያልታጠበ ቡሀቃ መስሏል።
ይህን ዓረፍተ ነገር ለየትኛው የድርሰት ዓይነት መነሻ ማድረግ ይቻላል?
ሀ. ለስዕላዊ ለ. ለተራኪ ሐ. ለአስረጅ መ. ለአመዛዛኝ

48. ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች መካከል የአመዛዛኝ ድርሰት መነሻ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?
ሀ. ውርጃ ማካሄድ በህግ መፈቀድ አለበት የሚሉ እናዳሉ ሁሉ ሊከለከል ይገባል የሚሉም አሉ።
ለ. ኢንጂነሩ የህዳሴን ግድብ የግንባታ ሂደት የተመለከተ ማብራሪያ ለጋዜጠኞች ሰጡ።
ሐ. ስምንተኛው አገር አቀፍ የሰንደቅ ዓላማ ቀን በአዲስ አበባ ስታዲየም በደማቅ ሂኔታ ተከብሮ
መዋሉ ተገለፀ።
መ. አካባቢውን አስተውሎ ለተመለከተው ጥሩ ሰዓሊ ተጠንቅቆ የሰራው ስዕል እንጂ በተፈጥሮ
የተገኘ አይመስልም።

49. ወጣ ወጣ ስትል ክፉ ምች መቷት
ተቸግሬያለሁኝ ያችን ልጅ አሚት። የዚህ ቅኔ ህብረቃል የትኛው ነው?
ሀ. ያችን ለ. ተቸግሬያለሁኝ ሐ. አሚት መ. መቷት

50. ኧረተው አንተ ሰው አትውረድ በደጄ
እንደ ገለባ እሳት ትጠፋለህ በጄ
ይህን ቃላዊ ግጥም የሚያንጎራጉረው ሰው ---------- ነው
ሀ. ግራ የገባው ለ. የከፋው ሐ. የደከመው መ. የራበው

51. አቀበት ቁልቁለት አይልም ጉልበቱ
ጥርሶችህ መካከል ይሰራልኝ ቤቱ
ይህ ቃላዊ ግጥም የትኛውን ይመለከታል?
ሀ. አፍቃሪን ለ. ሀሜተኛን ሐ. ሰራተኛን መ. ጀግናን

52. ካገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ
ቢጭኑት አህያ ቢጋልቡት ፈረስ
የዚህን ቃላዊ ግጥም መልዕክት የትኛው ምሳሌያዊ አነጋገር ይገልፃል?
ሀ. ሀገር ያለምክር፣ ቤት ያለማገር ሐ. የሰው መሰረቱ፣ እናትና አባቱ
ለ. አንበሳ በዱሩ፣ አዞባህሩ መ. አውቆ የሚያጠፋ፣ ኑሮው ምን ከፋ

53.የሆዴን እንፋሎት ጥርሴ እየመለሰው
እንደልቡ አዳሪ እመስላለሁ ለሰው
የሚለውን ቃላዊ ግጥም የሚያንጎራጉረው ---------- ነው
ሀ. የከፋው ሰው ለ. ያፈቀረ ሰው ሐ. ህመምተኛ ሰው መ. ነገረኛ ሰው

54.በግንቦት ጠሀይ ፈራ
በሀሀምሌ ዝናብ ፈራ
ልጁ እንጆራ ቢለው
በጅብ አስፈራራ የሚለው ቃላዊ ግጥም በውስጠ ታዋቂነት ለማን የተገጠመ ይመስላል?
ሀ. ለሰነፍ ገበሬ ለ. ለፈሪ አባወራ ሐ. ለከሰረ ነጋዴ መ. ለፈሪ ሰው ሁሉ

55.አታሞውን ምቺው ባንደኛው እጅሽ
አንጀት የሚበላ ወዳጅ እንዳለሽ
ይህ ቃላዊ ግጥም የሚዜመው እንዴት ላለች ሴት ነው?
ሀ. ዘመዷን በሞት ላጣች ሐ. በወዳጇ ፊት ለተነሳች
ለ. ፍቅር ለጠናባት መ. ከበሮ መምታት ለምትደሰት

56.እኔስ እሄዳለሁ እኖራለሁ የትም
እንግዲህ ለፍቅር ስራ አልፈታለትም
እየተጀመረ ለሚቀረው የትም ይህንን ቃላዊ ግጥም የሚያንጎራጉረው እንዴት ያለ ወጣት ነው?
ሀ. ፍቅረኛውን ዘመዶቹ የጠሉበት ሐ. ፍቅረኛው የራቀችው
ለ. በፍቅር ፍለጋ የተጠመደ መ. በዓይናፋር ፍቅረኛ የተማረረ

57.አንተ አትረስ ተወው ይረሰው ሃገሩ
እንዳይጎነትልህ ጓሉና አፈሩ
አንተ ተወውና ይረስ አባትህ
ጭቃ እንዳይለወስ ድንቡሌው ባትህ የሚለው ግጥም ለማን የተገጠመ ነው?
ሀ. ለሽሙንሙን ወጣት ሐ. ለድንቡሌ ባት
ለ. ለሰነፍ ገበሬ መ. በሀገሬው ለሚወደድ ሰው

58.አህያ መጣች ተጭና እንዶድ
ክፉ ቀን መጥቷል የሚያካክድ የሚለው ቃላዊ ግጥም መልዕክቱ ምንድን ነው?
ሀ. ጊዜው የረሀብና የችግር መሆኑን ማመልከት
ለ. የጊዜውን አስተማማኝነት መግለፅ
ሐ. ጊዜው ሰዎች ቃል የገቡትን እንዲፈፅሙ ማስቻሉን ማመልከት
መ. ጊዜው ሰዎች ቃላቸውን የማያከብሩበት መሆኑን ማመልከት

59.ደቦ አልገባ ብሎ ሂድ ወግድ ካላችሁ፣
ዶቃ ልቀም በሉት ወንዝ ውስጥ በትናችሁ።
ይህ ቃላዊ ግጥም የሚያስተላልፈው ምክር ምንድን ነው?
ሀ. መተባበር አስፈላጊ መሆኑን ሐ. ተንኮል መስራት መጥፎ መሆኑን
ለ. ባለወገን የሆነ ተጠቃሚ መሆኑን መ. እምቢተኛ መቀጣት ያለበት መሆኑን

60.‹‹ካለፈ በኋላ እንዳትናደዱ
ቁጣ ሲያገኛችሁ ትዕግስትን ውደዱ፡፡››
የዚህን ግጥም መልዕክት የሚገልፀው የትኛው ምሳሌያዊ አነጋገር ነው?
ሀ. ቁጥቋጦ ሲያድግ ዛፍ ይሆናል፡፡ ሐ. ሊያልፍ ውሃ አደረገኝ ደሃ፡፡
ለ. ቁጡና ብስጩ አልማችሁ ፍጩ፡፡ መ. ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ፡፡

61.የክረምቱ ዶፍ ብዙ ቤቶችን አፈራርሷል፡፡ ------- በርካታ ሰዎች ያለመጠለያ ቀርተዋል፡፡ በባዶ ቦታው ላይ መግባት ያለበት አያያዥ ትኛው ነው?
ሀ. በዚህም በዚያም ለ. በዚህ ሁኔታ ሐ. በዚህ ዓይነት መ. በዚህ ሳቢያ

62.‹‹ሰው በተፈጥሮው ምክንያታዊ ነው፡፡ ስለሆነም አውቆም ሆነ ሳያውቅ ለሚያጠፋው ጥፋት ኃላፊነትን ከመውሰድ ይልቅ ምክንያት መደርደር ይወዳል፡፡›› ከመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ወደ ሁለተኛው ዓረፍተ ነገር መሸጋገሪያ በመሆን ያገለገለው --- ነው
ሀ. ምክንያት ለ. ስለሆነም ሐ. አውቆም መ. አውቆም ሆነ ሳያውቅ

63.አንድ ግለሰብ ለመስሪያ ቤቱ ማመልከቻ ቢፅፍ ከሚከተሉት የማያስፈልገው የትኛው ነው?
ሀ. የማመልከቻው ምክንያት ሐ. ማመልከቻው የሚፃፍለት ድርጅት ስም
ለ. የማመልከቻው ዝርዝር ጉዳይ መ. የማመልከቻው የፕሮቶኮል ቁጥር

64.ጎመን ቀቅል አሉኝ ምንጊዜ ሊበስል
ይህንን ቀንጥሼ እዘልቀው ይመስል፡፡ የዚህ ቅኔ ሚስጥራዊ ፍቺ (ወርቁ) የትኛው ነው?
ሀ. ይህንን ክፉ ቀን ማለፍ ተስኖኛል፡፡ ሐ. ጎመን በልቼ አልጨረሰውም፡፡
ለ. ለመብሰል ብዙ ጊዜ ይፈጃል፡፡ መ. ጎመኑ ብዙ ስለሆነ ቀንጥሼ አልጨርሰውም፡፡

65.እገዛለሁ ብሎ ተስማምቶ ነበረ
መልካም በቅሎ ልጄ ሳይቀመጥ ቀረ፡፡ የዚህ ቅኔ ወርቅ ---------- ነው
ሀ. ደህና ያሰበውን ፣ በቅሎ ገዝቶ ሳይቀመጥ ቀረ
ለ. እንደ በቅሎ አድጎ የእድገቱን ፍሬ ሳይበላ ቀረ
ሐ. አስተዳደጉ ደህና መጥቶ ከፍፃሜ ሳይደርስ ተቀጨ
መ. የበቀለውን ሳር በቅሎ ሳትመገበው ቀረች

66.የኦልማ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት ዋና ዓላማ ተማሪዎችን በዕውቀት ከመቅረፅ ጎን ለጎን በመልካም ስነምግባር ኮትኩቶ ማሳደግ ነው፡፡ ይህ ዓረፍተ ነገር ከዓረፍተ ነገር ስልቶች ውስጥ በየትኛው ስር ሊመደብ ይችላል?
ሀ. ትዕዛዛዊ ለ. ጥያቄያዊ ሐ. አሉታዊ መ. አወንታዊ

67.ከሚከተሉት አንዱ በስራ ደብዳቤ መጀመሪያ ላይ ቀድሞ ይፃፋል
ሀ. ደብዳቤው ወጭ የተደረገበት የፋይል ቁጥር
ለ. ደብዳቤውን የላከው መስሪያ ቤት አድራሻ
ሐ. ደብዳቤውን የሚቀበለው መስሪያ ቤት አድራሻ
መ. ደብዳቤው የፃፈበት ምክንያት

68.እፀድቅ ብዬ ባዝላት ---------- ። ይህንን ምሳሌያዊ አነጋገር ሙሉ የሚያደርገው የቱ ነው?

ሀ.እንኮኮ አማራት ለ. አንቀልባ ፈለገች ሐ. ጭራሽ አለቀሰች መ. ተንጠልጥላ ቀረች

69.እርሙን አወጣ ከሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ጋር በፍቺ የሚስማማው ---------- ነው

ሀ. አለቀሰ ለ. ማለ ሐ. ታረቀ መ. ወቀሰ

70.ከሚከተሉት በመነሻውና በመድረሻው ላይ ቅጣይ ምዕላዶች የሌሉት ቃል የትኛው ነው?

ሀ. ቁርጭምጭሚት ለ. አይተባበሩም ሐ. አልሰረፀም መ. ከአንጀቴ

71.---------- እንደሚባለው ታላፊውን ከቁም ነገር ባለመቁጠር የታዘዘውን ስራ መስራት ትቷል።

ሀ. ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ሐ. ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ

ለ. አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ መ. አንድ ቀን ቢስቱ ዓመት ይፀፀቱ

72.ከፍተኛ በደል የደረሰበት የተሰማውን ብሶት ሳይገልፅ፣ ይህን ያህልም የከፋ ችግር ያልደረሰበት ሰው የበለጠ እንደተበደለ ሆኖ ቀረበ። ለዚህ ዓይነቱ ገጠመኝ ተስማሚ የሆነው ምሳሌያዊ አነጋገር የትኛው ነው?

ሀ. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች ሐ. ሞኝ የዕለቱን ብልህ ያመቱን

ለ. ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም መ. የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ

73.ከሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች መካከል አመዛዛኝ ድርሰት ለመፃፍ አመቺ ያልሆነው የትኛው ነው

ሀ. ለሴት ተማሪዎች የሚደረግ አዎንታዊ አድልዎ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል።

ለ. ሰው ሰራሽ መዳበሪያዎች ከጥቅማቸው ጉዳታቸው ይብሳል።

ሐ. ከባዕዳን ሀገሮች የሚመጡ ዕርዳታዎች ከድህነት የሚያላቅቁን አይደሉም።

መ. የገንዘብ አያያዝን በሚመለከት ጥሩ አመለካከት የሌላቸው መላጆች እንዴት ያሉ ናቸው

74.መምህሩ <u>እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ</u> ወደ ክፍል ገባ። የተሰመረበት ፈሊጥ ፍቺ

ሀ. ሲጋራ እያጨሰ ለ. ተደስቶ ሐ. ተናዶ መ. በእሳት ተቃጠለ

75.ለሶስት ቀናት ከገላዋ ያልወለቀ ሮዝ ፒጃማዋን ለብሳ ሶፋ ላይ ጋደም ብላለች። በአጫጭር ጣቶቿ ረጅም ፀጉሯን እየቧጠጠች ማስቲካ ያለእረፍት ታኝካለች።ጎላ ጎላ ያሉ ውብ ዓይኖቿ በናፍቆት ፍዝዝ ብለው ባዶውን ያያሉ። የሚለው ቅንጫቢ ሀሳብ ለትኛው የድርሰት ዓይነት ምሳሌ ይሆናል? ሀ. ተራኪ ለ. ገላጭ ሐ. ስዕላዊ መ. አመዛዛኝ

76.አዲስ አበባ ላይ ቡና ቢወደድ

ከጅማ ሰውካለ ይመጣል በግድ የዚህ ቅኔ **ወርቅ** የትኛው ነው?

ሀ.ጅማ የሚኖር ሰው ካለ ያመጣል። ሐ. ከዳተኛ (ከሀዲ) ሰው

ለ. ቡና አዲስ አበባ ውድ ነው መ. ጅማ ቡና ርካሽ ነው

77.በመሶቡ ሁሉ ይቅረብ እንጀራው

አስተዳዳሪያችን ሆደ ሰፊ ነው የዚህ ቅኔ **ህብረ ቃል** ትኛው ነው?

ሀ. አስተዳዳሪያችን ለ. ሆደ ሰፊ ሐ. እንጀራው መ. በመሶቡ

78.ወጣ ወጣ ስትል ክፉ ምች መቷት
ተቸግሬያለሁኝ ያችን ልጅ አሚት፡፡ የዚህ ቅኔ ሰም የትኛው ነው?
ሀ. ስሟን በክፉ አነሷት፡፡ ሐ. ልጅቷን ስላመማት ተቸግሬያለሁ
ለ. ምች መቷት ታማለች፡፡ መ. መልሰ አልተሰጠም፡፡

79.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ፣ አንድ መስሪያ ቤት የተለያዩ ጉዳዮች እንዲፈፀምለት ወደ ሌላ መስሪያ ቤት የሚፅፈው ነው፡፡
ሀ. የግል ማስታወሻ ለ. የውስጥ ማስታወሻ ሐ. የሰላምታ ደብዳቤ መ. የስራ ደብዳቤ

80.... ከዕለታት አንድ ቀን፣ ወደሱ ቀርቦ፣ እህቱ ልትዳር ስለሆነ መሄድ አለብኝ አለው፡፡
ከላይ ከቀረበው ሀሳብ ውስጥ በድርብ ትምዕርተ ጥቅስ ውስጥ መግባት ያለበት የትኛው ነው?
ሀ. ወደርሱ ቀርቦ እህቱ ልትዳር ስለሆነ መሄድ አለብኝ ሐ. ከዕለታት አንድ ቀን
ለ. እህቱ ልትዳር ስለሆነ መሄድ አለብኝ መ. መሄድ አለብኝ አለው

81.ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ወስጥ ባለፈ ነገር ላይ መቆጨት አላስፈላጊ መሆኑን የሚመክረው የትኛው ነው?
ሀ. የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም ሐ. ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኀኒቱ
ለ. ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ መ. ሀ ና ለ መልስ ናቸው

82.ካያያዝ ይቀደዳል ---------- ምሳሌያዊ አነጋገሩን ሊያሟላ የሚችለው የትኛው ነው?
ሀ. ካነጋገር ይፈረዳል ሐ. ካለባበስ ያምራል
ለ. ካለመናገር ይቀራል መ. ካለማወቅ ይቀራል

83.‹‹ፀሀይ ሳለች እሩጥ አባት ሳለ አጊጥ›› የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር መልዕክት ----------
ሀ. ሁሉንም ነገር በጊዜ አከናውን ሐ. ስራ ያለፀሀይ አይሆንም
ለ. በፀሀይ መሮጥ አሸናፊ ያደርጋል መ. ያለ አባት ስኬታማ መሆን አይቻልም

84.--------- ሞትን መሻገር ከተቻለ አዲስ ህይወትና እድል ይገኛል፡፡ --------- እንደሚባለው...
ለዓረፍተ ነገሩ ክፍት ቦታዎች ተገቢ የሚሆነው ስርዓተ ነጥብ የትኛው ነው?
ሀ. ቅንፍ ለ. ድርብ ትዕምርተ ጥቅስ ሐ. ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ መ. ነጠላ ሰረዝ

85.ተጋባዣዮ ተናጋሪ፣ መፅሀፍት የማንበብ ልምድን በሚመለከት ገለፃ አደረጉ፤ ---------
ስላነበቧቸው መፃህፍት አንዳንድ ነገር ተናገሩ፡፡ ክፍት ቦታውን ሊያሟላ የሚችለው አያያዥ
ሀ. ስለዚህ ለ. በመቀጠልም ሐ. ነገር ግን መ. ስለሆነም

86.የማይገናኝ ነገርን ለመግለፅ ሲፈለግ ---------- ይባላል፡፡
ሀ. ቀን እስኪያልፍ ያልፋል፡፡ ሐ. ሞኝ የዕለቱን ብልህ ያመቱን፡፡
ለ. ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ፡፡ መ. ከአፍ ከወጣ አፋፍ

87.ለአሉታዊ ዓረፍተ ነገር በምሳሌነት በምሳሌነት የትኛው ሊጠቀስ ይችላል?
ሀ. ጥያቄዎችን በተለያየ መንገድ መፃፍ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡
ለ. ጥያቄዎችን በተለያየ መንገድ ለመፃፍ ዝግጅት ያስፈልጋል፡፡
ሐ. ጥያቄዎችን በተለያየ መንገድ መፃፍ ይቻላል፡፡
መ. ጥያቄዎችን በተለያየ መንገድ መፃፍ አይከብድም፡፡

88.ከሚከተሉት አማራጮች ስነ ፅሁፍ ያልሆነው የትኛው ነው?
ሀ. መካር የሌለው ንጉስ ያለ አንድ ዓመት አይነግስ
ለ. ደቦ አልገባ ብሎ ሂድ ወግድ ካላችሁ
ዶቃ ልቀም በሉት ወንዝ ውስጥ በትናችሁ
ሐ. የቡሄ በሉ ግጥም
መ. ህዳሴ ግድብን በተመለከተ የተዘጋጀ ዘገባ

89.‹‹ግጥም በጥቂት ቃላትና መስመሮች ብዙ ለማለት የሚያስችል የስነ ፅሁፍ ዘርፍ ነው›› የሚለው ገለፃ ከስነ ግጥም ባህርያት መካከል በይበልጥ የትኛውን ይመለከታል?
ሀ. ምትን ለ. ዜማን ሐ. ምጣኔን መ. እምቅነትን

90.ትንፋሿ ሽቶ ነው ድምጿም የመረዋ
የሞተን ያስነሳል ደማቅ ፈገግታዋ
ይህ ግጥም ያካተታቸው ዘይቤዎች በተከታታይ ምንና ምን ናቸው?
ሀ. ግነት እና አነፃፃሪ ለ. ግነት እና ሰውኛ ሐ. ለዋጭ እና ግነት መ. ምፀት እና ለዋጭ

91.‹‹አንድ እንጀራ ራቴ መስታወቴ ነሽ፣
ከቶ የስንቱን ፊት ታሳይኛለሽ፡፡›› ይህ ቃላዊ ግጥም ምንን ይገልፃል?
ሀ. ናፍቆትን ለ. ቁጣን ሐ. ንዴትን መ. ብሶትን

92.‹‹ትንሽ ስጋ እንደ መርፌ ትወጋ›› ለሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር አቻ የሆነው የቱ ነው?
ሀ. ሰባራ ቂጣ አርባ ጅራፍ ታስቀጣ ሐ. ሀመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ
ለ. አፍንጫን ሲመቱት ዓይን ያለቅሳል መ. ድመት መንኩሳ አመሏን አትረሳ

93.ከሚከተሉት መካከል አንዱ የውይይት የመጨረሻ ግብ ነው
ሀ. አድማጭን ማሳመን ሐ. የጋራ መግባባት ላይ መድረስ
ለ. የሌሎችን አቋም ማስለወጥ መ. አቋምን ለሌላው አካል ማሳወቅ

94.በግጥም ውስጥ ሳድሶችን እንደ ቀለም የምንቆጥረው መቼ ነው?
ሀ. በቃል መነሻ ሲገኙ ለ. ጠብቀው ሲነበቡ ሐ. ተረግጠው ሲነበቡ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

95.‹‹እሱማ ጨዋ ነው ባህሉን አክባሪ
እርቃኑ ቢታይም ለብሶ ትልትል ሱሪ
በአመሉስ ቢሆን ከቶ ማን ያማዋል
ቁማር፣ መጠጥ እንጂ ምን ተገኝቶበታል፡፡››
ይህ ግጥም በምን ዓይነት ዘይቤ የቀረበ ነው?
ሀ. ምፀት ለ. ግነት ሐ. ለዋጭ መ. ተምሳሌት

96.ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትዕምርተ ጥቅስ አጠቃቀም የተከተለው የትኛው ነው?
ሀ. ‹‹መልካም አስተዳደር የዕድገት መሰረት ነው በማለት ተናገረ!››
ለ. ‹‹መልካም አስተዳደር የዕድገት መሰረት ነው፤›› በማለት ተናገረ!
ሐ. ‹‹መልካም አስተዳደር›› የዕድገት መሰረት ነው በማለት ተናገረ!
መ. መልካም አስተዳደር ‹‹የዕድገት መሰረት ነው፤›› በማለት ተናገረ!

97. አቶ ጫላ የሚላስ የሚቀመስ የሌላቸው ምስኪን ሰው ናቸው። ይባስ ብሎ ልጃቸው የጎረቤት ልጅ ፈንክቶ አንድ ሺ ብር ካሳ እንዲከፍሉ ተጠየቁ ይህንን የታዘቡ ጎረቤታቸው -------- ብለው ተረቱ።

ሀ. ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ ሐ. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

ለ. በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ መ. የረጋ ወተት ቅቤ ይወጠዋል

98. ‹‹አለመ›› የሚለው ቃል ‹‹አነጣጠረ›› የሚል ፍች የያዘው በየትኛው ዓ.ነገር ውስጥ ነው?

ሀ. ጫላ ማታ የማይሆን ህልም አለመ።

ለ. አብዲ የሀገሪቷ ሁኔታ ስላልተመቸው ከሀገር ለመውጣት አለመ።

ሐ. አዳኙ ሚዳቆዋን ለመምታት አለመ።

መ. በቀጣይ ዓመት አንዳች ነገር ለመስራት አለመ።

99. የአንድን ነገር ሁናቴ በዓይን እንዳዩት በእጅ እንደዳሰሱት በጆሮ በቅርብ ሆነው እንደሰሙት በጠቅላላው ግዙፍ አድርጎ የሚያቀርብ የድርሰት ዓይነት ---------- ይባላል።

ሀ. አመዛዛኝ ለ. ተራኪ ሐ. ገላጭ መ. ስዕላዊ

100. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በግጥም ውስጥ ቀለምን በተመለከተ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የተናባቢና የአናባቢ ቅንጅት ነው ሐ. ተናባቢ ብቻውን የሚፈጥረው ቅንጅት ነው።

ለ. አናባቢ ብቻውን የሚፈጥረው ቅንጅት ነው። መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

101. **አጠረ** ብሎ **አጭር** ካለ የሁለቱ የቃል ክፍል ልዩነት በቅደም ተከተል ----- እና ----- ነው

ሀ. ስም ና ቅፅል ለ. ግስ ና ቅፅል ሐ. ቅፅል ና ግስ መ. ቅፅል ና ስም

102. ‹‹የመስከረም ፀሀይ፣ ጥርሷን ለመፋቋ

እድል ለመንቃት፣ ዓለም ለመሳቋ ሐይወት ለመፍካት.... ›› በሚለው ውስጥ በጥቅም ላይ የዋለው የዘይቤ ዓይነት ሀ. ሰውኛ ለ. ግነት ሐ. አነፃፃሪ መ. ለዋጭ

103. ወጣቱ አንድ ጊዜ የጀመረውን ነገር ደጋግሞ በመስራት ለማሸነፍ ሰፊ የእድሜ <u>ገፀ በረከት</u> ያለው የህብረተሰባችን ክፍል ነው። በሚለው ዓረፍተ ነገር የተሰመረበት ቃል ፍች

ሀ. አቀማመጥ ለ. ችሎታ ሐ. ስጦታ መ. ምርቃት

104. ትልቅ ሀሳብ የሚለየው በሀሳብነቱ ---------- በአገላለፁ እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። በባዶ ቦታው ላይ መግባት ያለበት አያያዥ ቃል የቱ ነው?

ሀ. ይሁንእንጂ ለ. እንጂ ሐ. ነገርግን መ. ስለዚህ

105. ‹‹አህያውን ፈርቶ ዳውላውን›› ለሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ፍቺ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ. አጥፊውን ትቶ ያላጠፋውን ማጥቃት ሐ. ጥጋበኛ ሰው ቅጣት ይገባዋል

ለ. የረዳውን ትቶ ያልረዳውን ማጥቃት መ. አስፈላጊ ያልሆነን ነገር መነካካት

106. **የቀን ጅብ** ማለት ---------- ማለት ነው

ሀ. ስግብግብ ለ. ፈጣን ሐ. ጥጋበኛ መ. ልጓም የሌለው

107. ጠንክረህ አጥና ---------- ወድቀህ ትቀራለህ፡፡ በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ በባዶ ቦታው ላይ መግባት ያለበት አያያዥ
ሀ. ስለዚህ ለ. አለበለዚያ ሐ.ነገር ግን መ. ይሁን እንጂ

108. <u>ወጥ ረገጥ</u> መሆኑን ባውቅ ኖሮ ከእሱ ጋር ጓደኝነት አልመሰርትም ነበር፡፡
የተሰመረበት ፈሊጥ ፍቺ ሀ. ከዳተኛ ለ. ትዕቢተኛ ሐ. ባለጌ መ. ግፈኛ

109. እንደሱ ያለ <u>እንብርት የለሽ</u> ሰው አይቼ አላውቅም፡፡ የተሰመረበት ፈሊጥ ፍቺ
ሀ. ምስጢር የማይደብቅ ለ. የማይጠግብ ሐ. ቦርጫም መ. ሀሳብ የለሽ

110. ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ወሬኛነትን የሚነቅፈው የትኛው ነው?
ሀ. ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው ሐ. ለወሬ የለው ፍሬ
ለ. ሳያጣሩ ወሬ ሣይገድሉ ጎፈሬ መ. ሁሉም መልስ መሆን ይችላሉ

111. ከሚከተሉት ውስጥ የተለየ መልዕክት የያዘው ምሳሌያዊ አነጋገር የትኛው ነው?
ሀ. ካለመናገር ደኃዝማችነት ይቀራል፡፡ ሐ. በሽታውን የደበቀ መድሃኒት አያገኝም፡፡
ለ. ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይደርስም፡፡ መ. ዝምታ ወርቅ ነው፡፡

112. አቶ ገመቹ <u>ጥሮ ግሮ</u> የሚያድር ሰው ነው፡፡ የተሰመረበት ፈሊጥ ፍቺ
ሀ. ለፍቶ ለ. ተመሳስሎ ሐ. አስመስሎ መ. ተሸንፎ

113. አቶ ከበደ የልጅ ልጃቸውን ሲመክሩ፣ ‹‹በርታና ተማር ልጄ የተማረ ወድቆ አይወድቅም አይደል የሚባለው፤ እኔ አለመማሬ ብረሃን እንዳላይ አድርጎኛል፡፡›› ብለው ሳይናገሩ ቀርተው አያውቁም፡፡ በዚህ ሀሳብ ውስጥ በነጠላ ጥቅስ ውስጥ መግባት ያለበት የትኛው ነው?
ሀ. ተማር ልጄ ሐ. እኔ አለመማሬ ብረሃን እንዳላይ አድርጎኛል
ለ. የተማረ ወድቆ አይወድቅም መ. ልጄ የተማረ ወድቆ አይወድቅም አይደል የሚባለው

114. ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገር ውስጥ አንዱ ልዩ ነው
ሀ. የነቶሎ ቶሎ ቤት ግርግዳው ሰንበሌጥ ሐ. የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል
ለ. መቼ መጣሽ ሙሽራ መች ቆረጠምሽ ሽምብራ መ. የቸኮለች አፍስሳ ለቀመች

115. ‹‹ቅርብ ያለ ጠበል ልጥ ይነከርበታል፡፡›› የሚለው ምሳሌያዊ አነጋር አቻ
ሀ. ይሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ ሐ. አስር ያባረረ አንድ አይዝም
ለ. ምቀኛ የኑሮ መጋኛ መ. በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል

116. ---------- ዓይን ያለቅሳል፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሩን ማሟላት የሚችለው
ሀ. ያየውን አይቶ ለ. እግር ሲጎዳ ሐ. ልብ ሲያዝን መ. አፍንጫ ሲመታ

117. እናንተ ጌቶች ሆይ በምን ወጥ በላችሁ
እኛ በሹሮችን እናንተ በአሳችሁ የዚህ ቅኔ ህብረቃሉ የትኛው ነው?
ሀ. በሹሮችን ለ. እናንተ ሐ. በአሳችሁ መ. እኛ

118. የሰራውን ሰርቶ አበጀሁ ቢላችሁ
ይህን ባለ ጊዜ ምን ትሉታላችሁ የዚህ ቅኔ ሚስጥራዊ ፍቺ የትኛው ነው?
ሀ. የፈለገውን አድርጎ ደግ ሰራሁ ቢላችሁ ምን ትላላችሁ
ለ. የፈለገውን አድርጎ ደግ ሰራሁ ቢላችሁ ባለጊዜ ነውና ምን ማድረግ ትችላላችሁ
ሐ. ጥሩ ስራ ከሰራ ማመስገን እንጅ ሌላ ምን ትላላችሁ
መ. ስራውን ጥሩ አድርጎ ባይሰራም ማመስገን ተገቢ ነው፡፡

119. ‹‹ሰዎች መጥተው ነበር ጨኸቱን ሰምተው
ተመልሰው ሄዱ ይምታታ ብለው፡፡›› የዚህ ቅኔ ህብረ ቃል የትኛው ነው?
ሀ. ተመልሰው ለ. ሄዱ ሐ. ይምታታ መ. ጨኸቱን

120. የያዘኝ አባዜ እዩት ሲያዋርደኝ
ስንቱ አዳራሽ ሞልቶ ድንኳን ሲያስወድደኝ፡፡ የዚህ ቅኔ ሰም የትኛው ነው?
ሀ. ስንት ያማረ አዳራሽ እያለ እኔ ግን በድንኳን መሆንን መረጥኩ፡፡
ለ. ሰርግ ከመሄድ ይልቅ ለቅሶ መሄድ እወዳለሁ፡፡
ሐ. ስንት ረጅም ሴት እያለ በጣም አጭሯን ወደድኩኝ
መ. አዳራሹ ስለሞላ ድንኳን እንድገባ ተገደድኩኝ፡፡

121. ድርብ ትዕምርተ ጥቅስ በአግባቡ ጥቅም ላይ የዋለበት አረፍተ-ነገር የቱ ነው?
ሀ. ‹‹ጋሼ በጣም ታድለዋል የእርሶ ዓይነት ፀባይ የትም ዓይገኝም፡፡›› አልኳቸው፡፡
ለ. ጋሼ በጣም ታድለዋል ‹‹የእርሶ ዓይነት ፀባይ የትም ዓይገኝም፡፡›› አልኳቸው፡፡
ሐ. ‹‹ጋሼ በጣም ታድለዋል›› የእርሶ ዓይነት ፀባይ የትም ዓይገኝም፡፡አልኳቸው፡፡
መ. ‹‹ጋሼ በጣም ታድለዋል የእርሶ ዓይነት ፀባይ የትም ዓይገኝም፡፡ አልኳቸው፡፡››

122. ከሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ‹‹ተለማመጠ›› የሚል ፍቺ የያዘው የትኛው ነው?
ሀ. አፉን አሟሸ ለ. አንጀቱ ቆረጠ ሐ. መሬት ላሰ መ. ነፈረቀ

123. <u>ሸማውን ዘርግቶ</u> በሚያገኘው ገቢ ልጁን ያስተምራል፡፡ የተሰመረበት ፈሊጥ ፍቺ
ሀ. ተለማምጦ ለ. ለፍቶ ሐ. ለምኖ መ. ልብስ ሰፍቶ

124. ‹‹ስኳርን ባልወድ ለጤናዬ፣
ማር እባክህን ጌታዬ፡፡›› የዚህ ቅኔ ወርቅ (ሚስጥራዊ ፍች) የትኛው ነው
ሀ. ጌታዬ እባክህ የሚበላ ማር ስጠኝ፡፡ ሐ. ስኳር አልወድም ማር ይሰጠኝ፡፡
ለ. ጌታዬ እባክህ ይቅርታ አድርግልኝ፡፡ መ. ለጤናዬ ማር ስጣት፡፡

125. ‹‹እኔ የልጇ ልጅ እሷ የናቱ እናት
አኳኋኗ ሁሉ እንዳያት እንዳያት›› የዚህ ቅኔ ሰም
ሀ. ሁኔታዋ ሁሉ እንደ ትልቅ ሰው ነው ሐ. ተመልካች ትፈልጋልች፡፡
ለ. እንድመለከታት ትፈልጋለች፡፡ መ. እንዳያት ሆነች፡፡

126. ከሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች መካከል ‹‹ተጠላ›› የሚል ፍቺ ያለው የትኛው ነው?
ሀ. ፍርድ ለበሰ ለ. በነገር ወጋው ሐ. ጥርስ ገባ መ. ሰማይ ተደፋበት

127. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ‹‹ኩታ ገጠም›› ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ፍቺ የሚሆነው
ሀ. ድንበርተኛ ለ. ልብስ ሰፊ ሐ. ወሰንተኛ መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

128. ሁሉም መሳቂያ ነው ጊዜውን ሲስት
ብትር ቀን አያምርም ለሚመለከት የሚለው ቅኔ ወርቅ
ሀ. ዱላ መያዝ በቀን አያምርም ሐ. ብትሸሸን/ ከእኛ ብትርቅ/ አያምርም
ለ. ቀን አያማርርም መ. ሀ እና ለ

129. አበራሽ <u>**የሴት ቁንጮ**</u> ናት፡፡ የተሰመረበት ፈሊጥ ፍቺ
ሀ. ባለሙያ ለ. አስተዋይ ሐ. ታታሪ መ. ታላቅ እህት

130. ከግጥም ዓይነቶች ውስጥ የወል ቤት ግጥም በሀረግ ስንት ቀለም አለው?
ሀ. ስድስት ለ. አስራ ሁለት ሐ. አምስት መ. አስር

131. በዱልዱም ቢቀርፀት ብዕር አለቀሰ፣
ጥቁር ቀለም ሳይሆን ደም እያፈሰሰ፡፡ የሚለው ግጥም ከየትኛው የግጥም ዓይነት ይመደባል?
ሀ. ሆያ ሆዬ ለ. ሰንጎ መገን ሐ. ቡሄ በሉ መ.የወል ቤት

132. ለራሱ እንጂ ለሌላ የማይሆን ዓይነት ሰውን ባህርይ ለመግለፅ የትኛው ምሳሌያዊ አባባል ይቀርበዋል?
ሀ. የሸማ ጥቅል የወርቅ እንክብል
ለ. የእንጨት ምንቸት እራሱ አይድን ሌላውን አያድን
ሐ. የሸንበቆ በትር ቢመረኮዙት ይሰበራል፣ ቢመቱበት እጅ ያቆስላል
መ. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል

133. ‹‹ወደ ኋላ የማይል›› የሚለውን ፍች ሊያስገኝ የሚችለው ፈሊጣዊ አባባል የትኛው ነው?
ሀ. ግንባር ለግንባር ሐ. ግንባረ ደረቅ
ለ. ግንባሩ የማይታጠፍ መ. የጦር ግንባር

134. ጭራሽ ሰነፍ የሆነን ሰው መግለፅ ቢያስፈልግ የትኛውን ፈሊጣዊ አባባል መጠቀም ይሻላል?
ሀ. እጀ ሰባራ ለ. እጅ አደር ሐ. እጁን ከብብቱ አገባ መ. እጁ አመድ አፋሽ

135. ከሚከተሉት ፈሊጣዊ አባባሎች መካከል ‹‹ጮሌ›› የሚል ፍች የሚኖረው የትኛው ነው?
ሀ. እሳት የላፊው ለ. በደረቁ ላጨ ሐ. አንደበተ ስል መ. ነገር ሰራ

136. ተጨዋቾቹ ወደ <u>መልበሻ</u> ክፍል ገቡ፡፡ የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍሉ -------- ነው
ሀ. ግስ ለ. ቅፅል ሐ. ስም መ. ተውሳከ ግስ

137. ከግስ ለተመሰረቱ ስሞች ምሳሌ የማይሆነው የቱ ነው?
ሀ. አለባበስ ለ. መልበስ ሐ. አመራረጥ መ. ቤት

138. በግጥም ውስጥ ቀለም ማለት ---------- ነው
ሀ. የአናባቢና የተነባቢ ድምፆች ቅንጅት ሐ. ሀ ና ለ መልስ ኖቸው
ለ. አናባቢ ድምፅ ብቻውን ሲመጣ መ. መልስ የለም

139. ቀጥሎ የቀረበው ግጥም ከየትኛው የግጥም ዓይነት ይመደባል?
‹‹ሆኖ ከተገኘ ሰው የክፋት ዋሻ
ወዳጅ አያስመኝም እስከመጨረሻ፡፡››
ሀ. የወል ቤት ለ. የሰንጎ መገን ቤት ሐ. ቡሄ በሉ ቤት መ. የፀጋዬ ቤት

140. እዛ ማዶ ጭስ ይጨሳል
አጋፋሪ የደግሳል፡፡ ይህ ግጥም ከየትኛው የግጥም አይነት ይመደባል?
ሀ. የወል ቤት ለ. ቡሄ በሉ ሐ. ሰንጎመገን መ. የፀጋዬ ቤት

141. ‹‹ጅብን ፈርቼ ከዛፍ ብወጣ ነብር ቆየኝ፡፡›› ለሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር የትኛው ይስማማል?
ሀ. ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም፡፡ ሐ. የባሰ አለ አገርህን አትልቀቅ፡፡
ለ. አውሬ ከዋሻ፣ በሬ ከእርሻ፡፡ መ. ብነጨው ፊቴን፣ ብመታው ደረቴን፡፡

142. የውስጥን አውጥቶ በመናገር መፍትሄ ሊገኝ መቻሉን የምንገልፀው በየትኛው አባባል ነው?
ሀ. ከፎከረ የጠረጠረ ይሻላል፡፡ ሐ. ካልደፈረሰ አይጠራ፣ ካልጠራ አይጠጣም፡፡
ለ. ካላስተዋሉ፣ አይገኝ ሁሉ፡፡ መ. ህመሙን የደበቀ መድሃኒት የለውም፡፡

143. ‹‹ሰነፍ እረኛ ከሩቅ ይመልሳል፡፡›› የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ፍቺ
ሀ. ሰነፍ ጠንቃቃ ነው
ለ. ሰነፍ እራሱን ከነገር ያርቃል
ሐ. ሰነፍ ሰው ነገሮችን ከርቀት ይቆጣጠራል፡፡
መ. ሰነፍ ስራውን የሚሰራው እያከማቸ ነው፡፡

144. ከሚከተሉት ውስጥ በደብዳቤ አፃፃፍ ስርዓት መሰረት ለሁሉም የደብዳቤ ዓይነቶች የጋራ ያልሆነው የትኛው ነው?
ሀ. ቁጥር ለ. ቀን ሐ. የተቀባይ አድራሻ መ. የላኪው አድራሻ

145. ‹‹ንፋስ በዓይን የማይታይ በእጅ የማይዳሰስ ሲነፍስ ስሜቱ ለፍጥረት ሁሉ የሚሰማ ነው፡፡›› ይህ ዓረፍተ ነገር ከነማብራሪያው ቢፃፍ ለየትኛው የድርሰት ዓይነት ምሳሌ ይሆናል
ሀ. ገላጭ ድርሰት ሐ. ስዕላዊ ድርሰት
ለ. አመዛዛኝ ድርሰት መ. ተራኪ ድርሰት

146. የክረምቱ ዶፍ ብዙ ቤቶችን አፈራርሷል፡፡ ------- በርካታ ሰዎች ያለመጠለያ ቀርተዋል፡፡ በባዶ ቦታው ላይ መግባት ያለበት አያያዥ ትኛው ነው?
ሀ. በዚህም በዚያም ለ. በዚህ ዓይነት ሐ . በዚህ ሁኔታ መ. በዚህ ሳቢያ

147. ‹‹ሰው በተፈጥሮው ምክንያታዊ ነው፡፡ ስለሆነም አውቆም ሆነ ሳያውቅ ለሚያጠፋው ጥፋት ኃላፊነትን ከመውሰድ ይልቅ ምክንያት መደርደር ይወዳል፡፡›› ከመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ወደ ሁለተኛው ዓረፍተ ነገር መሸጋገሪያ በመሆን ያገለገለው --- ነው
ሀ. ምክንያት ለ. ስለሆነም ሐ. አውቆም መ. አውቆም ሆነ ሳያውቅ

148. የግጥም ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ. ቁጥብ አይደለም ለ. ምት አለው ሐ. ዜማ አለው መ. ምጣኔ አለው

149. ግጥም ተለከክቶ የሚያልቀው በምን ውስጥ ነው?
ሀ. በስንኝ ለ. በቀለም ሐ. በቤት መ. በሐረግ

150. ‹‹በአሁኑ ወቅት በሀገራችን የተከሰተውን የኮሮና ወረርሽኝ ለመግታት ከእያንዳንዳቸን ምን ይጠበቃል ›› የሚለው ዓረፍተ ነገር ከዓረፍተ ነገር ስልቶች በየትኛው ስር ይመደባል?
ሀ. ሀተታዊ አወንታ ለ. ሀተታዊ አሉታ ሐ. ትዕዛዛዊ መ. ጥያቄያ

የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

መልመጃ አንድ

1. ሰንጎ መገን	2. ወል ቤት	3. ቡሄ በሉ
4. ወል ቤት	5. ሰንጎ መገነ	

መልመጃ ሁለት

ተራ. ቁ	ቃል	ነባ ምዕላድ	ጥገኛ ምዕላድ	የቅጥያ ምዕላዱ ተግባር
11.	ዘመናዊ	ዘመን	-አዊ	ቃል መስራት
12.	ኮታቸው	ኮት	-አቸው	ባለንብረትነት አመልካች
13.	ድንጋያማ	ድንጋይ	-አማ	ቃል መስራት
14.	ሙሽሪት	ሙሽራ	-ኢት	ያታ አመልካች
15.	ከብቶች	ከብት	-ኦች	ብዛት አመልካች
16.	ጨረቀዋ	ጨረቃ	-ዋ	እምርነትን አመልካች
17.	ተግባራት	ተግባር	-ኣት	ብዛት አመልካች
18.	ልብሳችሁ	ልብስ	-አችሁ	ባለንብረትነት አመልካች
19.	መስኮቶች	መስኮት	-ኦች	ብዛት አመልካች
20.	ኢትዮጵያዊ	ኢትዮጵያ	-ዊ	ወገን አመልካች

መልመጃ ሰባት

1. ቅፅላዊ	2. ተውሳከ ግሳዊ	3. ስማዊ	4. ስማዊ	5. መስተዋድዳዊ
6. ቅፅላዊ	7. ቅፅላዊ	8. ግሳዊ	9. ግሳዊ	10.ግሳዊ

መልመጃ ዘጠኝ

1. ሐተታዊ አወንታ	2. ትዕዛዛዊ	3. ትዕዛዛዊ
4. ጥያቄያዊ	5. ሀተታዊ አሉታ	6. አጋናኝ

መልመጃ አስራ ሁለት

1. በአረም ይመለሱ
2. ጥርስ አይሳበርም
3. የዝንብ መጫወቻ ይሆናል
4. ሲይዙት ያደናገር
5. በልጥ በረየ
6. በብልሃት
7. መልካም ወጥ
8. መልካም ሚስት
9. ሁለት ጉድጓድ
10. ሌባ ለአመሉ

የጥያቄዎች መልስ

1. ሐ
2. ሀ
3. ለ
4. ሀ
5. መ
6. ሀ
7. መ
8. ሀ
9. ሀ
10. ሐ
11. ሀ
12. መ
13. ለ
14. ሐ
15. ሐ
16. ለ
17. ሀ
18. ሀ
19. ለ
20. ሐ
21. ሐ
22. መ
23. ለ
24. ሐ
25. ለ
26. መ
27. ሐ
28. ሀ
29. ለ
30. ለ
31. ሐ
32. ሐ
33. ሐ
34. መ
35. ሀ
36. መ
37. መ
38. ሐ
39. ለ
40. መ
41. ለ
42. ለ
43. ሀ
44. ሐ
45. መ
46. መ
47. ሀ
48. ሀ
49. ሐ
50. ለ
51. ሀ
52. ለ
53. ሀ
54. ሀ
55. ሀ
56. ሐ
57. ሀ
58. መ
59. ሀ
60. መ
61. መ
62. ለ
63. መ
64. ሀ
65. ሐ
66. መ
67. ሀ
68. መ
69. ሀ
70. ሀ
71. ሐ
72. መ
73. መ
74. ሐ
75. ሐ
76. ሐ
77. ለ
78. ለ
79. መ
80. ለ
81. መ
82. ሀ
83. ሀ
84. ለ
85. ለ
86. ለ
87. መ
88. መ
89. መ
90. ሐ
91. መ
92. ለ
93. ሐ
94. መ
95. ሀ
96. ለ
97. ሐ
98. ሐ
99. መ
100. ሐ
101. ለ
102. ሀ
103. ሐ
104. ለ
105. ሀ
106. ሀ
107. ለ
108. ሐ
109. ለ
110. መ
111. መ
112. ሀ
113. ሐ
114. መ
115. መ
116. መ
117. ሐ
118. ለ
119. ሐ
120. ሀ
121. ሀ
122. ሐ
123. ሐ
124. ለ
125. ሀ
126. ሐ
127. ሀ
128. ሐ
129. ሀ
130. ሀ
131. መ
132. ለ
133. ለ
134. ሐ
135. ሀ
136. ሐ
137. መ
138. ሐ
139. ሀ
140. ለ
141. ሐ
142. መ
143. መ
144. ሀ
145. ሀ
146. መ
147. ለ
148. ሀ
149. መ
150. መ